
# አስተምህሮ ክርስቶስ

የክርስቲያናዊ አስተምህሮአገልግሎት

Teaching Christian Ministry



TCM

# Christology

# ማውጫ


1. መግቢያ
2. የክርስቶስ ህሉና
   2.1. በቅድመ ዘላለማዊነቱ
3. ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ
   3.1. አምሳያዊ ግለጠቱ
   3.2. ትንቢታዊ ንግርቱ
4. ተሰግዖ (ቃል ሥጋ/ሰው የመሆኑ ሚስጥር)
5. የክርስቶስ ማንነት
   5.1. ፍጹም መለኮትነቱ እና ፍጹም ሰውነቱ
   5.2. ክርስቶስ ራሱን ባዶ ማድረጉ [Kenosis ] ኪኖሲስ
   5.3. ክርስቶስ ኃጢያት ሊያደርግ አለመቻሉ
   5.4. በክርስቶስ ማንነት ላይ የተነሱ የስህተት ትምህርቶች
6. የክርስቶስ ባህርይ እና ስሞቹ
   6.1. ባህርይው
   6.2. ስሞቹ
7. የክርስቶስ ስራዎች
   7.1. በቅድመ ዘላለማዊነቱ
   7.2. በምድር ለ33 ½ ሲኖር
   7.3. ከትንሣኤው በኋላ
8. አስተምህሮ ክርስቶስን አስመልክቶ በተሳሰበተ የአተረጓጎም ምክንያት በተለየ ፍቺ የሚታዩ የምጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

# 1. መግቢያ

በወንጌላዊያን አማኞች ቤተ ክርስቲያን□እና በሌሎች ቤተ እምነቶች መከከል ልዩነት ከሚፈጠርባቸው መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች መከከል አንዐ ና ዋነኛው ስለ ክርስቶስ ማንነት ያለን አስተምህሮ ነው:: ስለሆነም በቤተ ክርስቲያናችን በክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑ አማኞች ስላመኑበት ጌታ□ጁበልጡን □እንዲገነዘቡና □እንዲያውቁ ለማድረግ ጁህ «ስተምህሮ ክርስቶስ» በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ትምህርት ጥሩ ግንዛቤን ያስጨብጣል::

ክርስቶስን ማወቅ የዘላለም ሕይወት ነው (ዮሐ17:3):: ጌታ□በምድር በነበረበት ጊዜ □እርሱን እንዲያውቁት በብዙ መንገድ እራሱን ይገልጥላቸው ነበር:: ይሁን □እንጂ ብዙዎቹ □እርሱን በማንነቱ ለመቀበል ተቸገረው ነበር:: ስለዚህም ለብዙዎቹ ግንበኞች የናቁት □እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ የተባለው ተፈጸመባቸው:: ያወቁትና ያመኑበት ደግሞ የዘለዓለምን ብፅዕናን አግኝተዋል:: ዛሬም ቢሆን ይህ እውነት እንዳለ ነው:: በክርስቶስ ማንነት ግራ ሳይጋቡ ያመኑበት በረከትን ሲጸኖፑ የማያምኑበት ደግሞ ከዚህ የዘላለም በረከት ጎድለዋል::

በክርስቶስ ኢየሱስ □እምነት ላሉም ሁሉ □እርሱን አውቀውት □እንደማይጨረሱ እንደማያልቅም ሁሉ ዛሬም በምንማረው ትምህርት □እርሱን አውቀነው አንጨርሰውም:: ላመንበት እውነት □እስከ ፍጻሜው ድረስ መቆም □እንድንችል መሰረታዊ □እውነቶችን □እንመለከታለን እንጂ::□እርሱን ባቀወቅነው መጠን ግን ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድነት □እንዲሁም □እርሱን ወደ መምሰል ሕይወት በምናደርገው ጉዞ ውስጥ ትልቅ በረከት በሕይወታችን □እናገኛለን::

ስለሆነም በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ተማሪዎች የሆናችሁ ሁሉ በቅን ልቦና □እንደ ቤሪያ ሰዎች ቃሉን □እየመረመራችሁ ለምትሰሙት □እውነት ፍጹም መታ□□ ለእግዚአብሔር፣ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን □እንዲሁም ለአገልጋዮቿ እንድታሳዩ ላሳስባችሁ እወዳለሁ::

□እግዚአብሔር ይባርካችሁ !

# 2. የክርስቶስ ህሉና

## (በቅድመ ዘላለማዊነቱ)

ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ሕሉና መቼ □እና □እንዴት ብሎ መጠየቅ ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን መመልስ አይቻልም:: መ□ሐአ ቅዐ ስ በቀዓ ታ□የሚያስቀምጥልን ጭብጥ ሀሳብ □እርሱ □ላለማዊ ነው የሚለውን ነው:: ይህም ሲባል መጀመሪያም መጨረሻም የለውም ማለቱ ነው:: በ□ህ ርክስ ስር ጸለዉን ሐሳብ ከመለዋወጣችን በፊት "ህሉና" የሚለውን ቃል ስለምን መጠቀሙ አስፈላጊ እንደ ሆነ መጠነኛ ግንዛቤን መስጠት እውደላሁ:: ስለ እግዚአብሔር መኖር ለመግለጽ ስንፈልግ የምንጠቀመው ቃል "ሕልውና" የሚለውን ሲሆን በእርግጥ "መገኘት" የሚለወን ሐሳብ የበለጠ ያብራራል ቃሉ:: "Existence" የሚለውን ለመግለጥ ግን ህሉና በቂ እና አቅም ያለው በመሆኑ ምክንያት ነው::

- ወንጌላዊው ዮሐንስ በጻፈው የወንጌል መልዕክቱ ላይ ምዕ 1:1-2 «**በመጀመሪያዉ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም □እግዚአብሔር ነበር::**» ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ህሉና ሚናገሩ ቃላትን ገና ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ማግኘት እንችላለን::
- _በመጀመሪያ ቃል ነበር ይለናል_:: ተፈጠረ ወይም ጅማሬ አለው አይልም □ቃላት አገባቡ በራሱ የሚያመለክተው ሃለፊ ጊዜን ነው «ነበር» ይለናል:: የነበረበትን ሁናቴ ሲቆል□ም ቃል ጁለ□ል:: ምን ማለቱ ነው? ዮሐንስ መልዕክቱን የሚጽፈው ለግሪክዊያን በመሆኑ ምክንያት ከእነርሱ አመለከከት አንጻር ተነስቶ ክርስቶስን ለማሳየት ነው የሚሞክረው ይህም ደግሞ ስለ ፍጥረት አመጣጥ የሚያምኑበት ሃሳብ አላቸው «ይህ የምንመለከተወ ዓለም የመጣው ቃል ወይም ሎጎስ ነው ምክኒያቱ» ብለው ያምናሉ:: ለእነርሱ ሎጎስ ማንነትን የተላበሰ ወጁም እኔነት ያለው በተጨማሪም የአምላክነትን ባሕሪ የተላበሰ ሳይሆን□□ኃይል ስራን ሊሰራ የሚችል መመሪያ እንደ እሆነ አድርገው ያምናሉ:: ዮሐንስ ከዚህ በመነሳት አስቀድሞ የነበረ ማንነትን የተላበሰ ከማንም በፊት የነበረ አድርጎ ክርስቶስን ለእነርሱ ለመመስከር በተጠቀመበት መንገድ ጸቀርበ□ል:: ዮሐ8፡56-59፡- "አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ አየም ደስም አለው::አይሁድም ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት::ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው:: ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ::"

  ራዕ1፡8፡- "ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ:: አልፋና ያሜጋ እኔ ነኝ ይላል::"

- _በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር::_ `` **In the beginning was the word ,and the <u>Word was with God</u>, and the Word was God. <u>He was in the beginning with God</u>`` John 1:1-2**

ዮሐንስ ይህ ቃል በሚል ማንነት የነበረ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር የሚኖረው በሚል ሌላ ተጨማሪ ሐሳብ ንግግሩን ያሳድገዋል። ቅድመ አኗኗሩ በራሱ አብሮነትን ሁሉ ያከተተ ነው። ከማን ጋር የሚልውን ለመመለስ በዚህ የንባብ ክፍል መሰረት መልሱ ከእግዚአብሔር ጋር ይለናል።ይህንን ሃሳብ ለማጠናከር በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 18 □እንመልከት «... **በአባቱ □እቅአ ጸለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።»** ጁህ እቅአ □ሚለዉ ቃል መሰረታዊ ሐሳብ አብሮነትን ነው □ሚጸመለ□ተዉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህንኑ ቃል በሌላ ስፍራም በዚሁ መሰረታዊ ሀሳብ ጁቷቀምበታል (ሉቃ16:19-31) ባለዉ ታሪ□ ውስጥ ድሃው ሰው በሞተ ጊዜ መላዕክት ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ይለናል።ይህ ማለት አብርሃም ወደ ነበረበት ወደ ጻድቃን ሕብረት ገባ ለማለት ነው የምሳሌው አገላለጽ።

- *<u>ቃልም እግዚአብሔር ነበር ።</u>* ይህ ቃል በሚል ማንነት ከእፀ□አብሔር ጋር ይኖር የነበረው ራሱም እግዚአብሔር ነበር ። ይህም ቃል አምላክ ነበር ለማለት ነው ዮሐንስ □□ለቶዉ።□እንግዲህ በጥቅሉ በዮሐንስ አቀራረብ መሰረት ቃል በሚል ማንነት ይኖር የነበረው መለኮትነት ባሕሪ ያለው በራሱም □እኔነት ያለው አምላክ ነው ይለናል። ስለዚህ ክርስቶስ በሕሉናው አስቀድሞም የነበረ ዓምላክ ነው። በመሆኑም ቃል የሚለውን የቅደም ኢየሱስ ክርስቶስ መጠሪያ ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃል አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይሆንም። ለምሳሌ በመዝሙር 32፡6 "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፤" የሚለው ሐሳብ "ቃል" ከሚለው ከቅድመ ክርስቶስ መጠሪያ እና ማንነት ጋር ከአፉ የሚወጣ ነበር ከሚል ሐሳብ ጋር ግንኙነት የለውም።
- ሐዋርያው ጳዉሎስ የክርስቶስን ቅድመ አኗኗር በቆላስይስ መልዕክቱ ላይ በግልጽ አስቀምጦአል። "...እርሱም ከሁሉ በፊት ነው..." (ቆላ 1፡17) በማለት።
- "ቃል" - በሚል የሚጠራው ከስላሴ አካላት አንዱ የሆነው እርሱም ራሱ **አምላክ** ነበር (መለኮት ነው) ስንል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ የምንባብ ክፍሎችን መመልከቱ ተገቢ ነው።
- ዕብ1፡5-14

  " ስለ ልጁ ግን። **አምላክ** ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው።ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው፤እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም
- ሮሜ 9፡5

  " አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም **የተባረከ አምላክ** ነው፤ አሜን።"

- 1ዮሐ5፡20

"የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ **እውነተኛ አምላክና** የዘላለም ሕይወት ነው።"

# 3. ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ

እግዚአብሔር አብን ያየው አንድስ እንኳ የለም። ምክንያቱ ደግሞ የሰዎች ልጆች በኃጢያት ምክንያቱ የእግዚአብሔር ክብር ከተለያቸው ጊዜ ጀምሮ በሥጋዊ አይኖቻቸው ልዑልን የማየት ብቃታቸው ስለ ጠፋባቸው ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች በክርስቶስ ይገለጣል ክርስቶሰም የእግዚአብሔር ብቸኛ መገለጫ መንገድ ነው።ይህ ማለት ከስላሴ አካላት አንዱ የሆነው ቃል (ወልድ) የእግዚአብሔር መታያ መንገድ ነው።ይህንንም ሁኔታ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ዘገባው ውስጥ አምሳያዊ ግልጠቱን እና ትንቢታዊ ንግርቱ ውስጥ እንዴት እንደ ነበር በእርግጥ ማየት ይቻላል።

**አምሳያዊ ግለጠቱ**

***ሀ. ቲዮፋኒ***

ክርስቶስ ወይም "ቃል" በብሉይ ኪዳን ይገለጥ ነበር ይህንን ግልጠቱን ለማጥናት አምሳያዊ ግልጠቱ በሚል ጽንሰሀሳብ ውስጥ አካተን መመልከት እንችላለን ይህም ግልጠቱ በሥነ-መለኮታዊ ቋንቋ ቴዮፋኒ ይባላል። ቲዮፋኒ ማለት ከግሪክ የመጣ ቃል ሲሆን ከሁለት የግሪክ ቃላቶች ማለትም "ቴዮ" እግዚአብሔር (አምላክ) ፣ "ፋኒ" መታየት ፣መገለጥ፣ ብቅ ማለት ሲሆን ሙሉ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ታየ ወይም ተገለጠ ለማለት የተሰጠ ስያሜ ነው። ይህም ሁኔታ ክርስቶስ ("ቃል") በሚታይ አካል በብሉይ ኪዳን ይገለጥ እንደ ነበር የሚያሳይ አገላለጥ ነው።ይህም ደግሞ በተለይ ክርስቶስ በሰው እና በመልአክ ተመስሎ መገለጡን ለማስረዳት የምንጠቀምበት ሀሳብ ነው።
በተለይ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሐዋርያው ጳውሎስ የተጠቀሱ ሐሳቦችን ቅድሚያ በመስጠት እንመልከት።

- ✓ 1ቆሮ10፡3-4

"ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፥ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ።"

ይህ ሀሳብ ጳውሎስ ለጣዖት የተሰዋን ስጋ መብላት ወይንስ አለመብላት በሚል ከቆሮንቶሳዊያን ለቀረበለት ጥያቄ መልስ በሰጠበት ክፍል ነው የሚገኘው። ነገር ግን በዚህ ውስጥ እንደምንረዳው

***ክርስቶስ የቀደሙትን የእምነት አባቶቻችንን በምድረ በዳው ጉዞ ወቅት አብሮአቸው እንደነበር መረዳት እንችላለን፡፡***

✓ ዕብ11፡ 25-26

**"ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኵር ብሎ ተመልክቶአልና፡፡"**

***የዕብራዊያኑ ጸሐፊ በእምነታቸው ወደኂላቸው ላፈገፈጉት አማኞች የቀደሙትን የእምነት አርበኞች ስል እምነታቸው ብርታት አንስቶ ሲናገር ሙሴ የግብጽ ፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል የወጣው ክርስቶስን በእምነት ተመልክቶ እንደነበር ያወሳል፡፡ይህም በቀደሙ የእግዚአብሔር ሰዎች ፊት ክርስቶስ እንደ ነበር የሚያሳይ ክፍል ነው፡፡***

✓ ኢሳ6፡1-13 ፤ዮሐ12፡37-43

***"ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፤ ስለ እርሱም ተናገረ፡፡" የኢሳይያስን ትንቢት እና የሐዋርያው ዮሐንስን የወንጌል ክፍል እጅግ አስገራሚ የሆነ አንድነት ያለው ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም ኢሳይያስ ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ያላወን እግዚአብሔርን አየ፤ ሲልን ዮሐንስ በወንጌሉ ደግሞ ኢሳይያስ የተመለከተው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ተብሎ የተገለጠውን ኢየሱስን ነው ብሎ ይለናል፡***

***ለመንደርደሪያነት እነዚህን ክፍሎች አነሳን እንጂ ክርስቶስ ("ቃል") በብሉይ ኪዳን እንደ ሰው እና እንደ መልዓክ የተገለጠባቸውን ክፍሎች ቀጥለን ደግሞ እንመለከታለን፡፡***

- ***እንደ እግዚአብሔር መልአክ***
  - ዘፍ16፡7-13፤21፡17 - ከአጋር ጋር

*"የእግዚአብሔር መልአክም* በውኃ ምንጭ አጠገብ በበረሀ አገኛት ምንጩም ወደ ሱር በምትወስደው መንገድ አጠገብ ነው።እርሱም፦ የሦራ ባሪያ አጋር ሆይ፥ ከወዴት መጣሽ? ወዴትስ ትሄጃለሽ? አላት። እርስዋም፦ እኔ ከእመቤቴ ከሦራ የኮበለልሁ ነኝ አለች። *የእግዚአብሔር መልአክም፦* ወደ እመቤትሽ ተመለሺ፥ ከእጅዋም በታች ሆነሽ ተገዥ አላት *የእግዚአብሔር መልአክም፦* ዘርሽን እጅግ አበዛለሁ፥ ከብዛቱም የተነሣ አይቆጠርም አላት። *የእግዚአብሔር መልአክም* አላት፦ እነሆ አንቺ ፀንሰሻል፥ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ ስሙንም እስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ፥ እግዚአብሔር መችገርሽን ሰምቶአልና።እርሱም የበዳ አህያን የሚመስል ሰው ይሆናል እጁ በሁሉ ላይ ይሆናል፥ የሁሉም እጅ ደግሞ

በእርሱ ላይ ይሆናል እርሱም በወንድሞቹ ሁሉ ፊት ይኖራል። እርስዋም ይናገራት የነበረውን **የእግዚአብሔርን ስም ኤልሮኢ** ብላ ጠራች የሚያየኝን በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን? ብላለችና።"

***በዚህ ክፍል ውስጥ ልብ ብለን ከተመለከትነው ከእመቤቷ ከሦራ ለኮበለለችው አጋር የተገለጠላት የእግዚአብሔር መልአክ ነው፤ በንግግራቸውም መሐል ጸሐፊው የእግዚአብሔርም መልአክ እያለነው የዘገበው ነገር ግን አጋር ያናግራት የነበረውን ስም ስትጠራ በእርግጥ መልአክ ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን ገልጣለች፡፡***

– **ዘፍ22፡11-18 - *አብርሃም ልጁን እንዳይሰዋ***

"*<u>የእግዚአብሔር መልአክም</u>* ከሰማይ ጠራና። አብርሃም አብርሃም አለው እርሱም፦ እነሆኝ አለ። እርሱም፦ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህን **ለእኔ አልከለከልህምና** እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ። አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው። አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል። *<u>የእግዚአብሔር መልአክም</u>* አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፥ እንዲህም አለው፦ እግዚአብሔር፦ በራሴ ማልሁ ይላል ይህን ነገር አድርገሃልና፥ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና።"

***በአብርሃም ልጅህን ሰዋልኝ ላላው ለአምላኩ ታዞ በሞሪያ ምድር ባለው ተራራ ላይ መሰዊያን አዘጋጅቶ ሊሠዋው በተዘጋጀ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከተሰማይ ተጠራና አትሰዋ አለው፡፡ በንግግሩ መሐል ግን የተገለጠው መልአክ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና ብሎ ሲል በእርግጥ ይህን የመሰለ ንግግር አንድ መልአክ ሊናገር እንደማይችል ይሉቁን ሰዋልኝ ብሎ ያዘዘው አምለኩ መሆኑን "ለእኔ" የሚለው ቃል ገለጭ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡***

– ዘፍ31፡11 - ያዕቆብን የረዳው

*<u>"የእግዚአብሔርም መልአክ</u>* በሕልም። ያዕቆብ ሆይ አለኝ እኔም። እነሆኝ አልሁት። እንዲህም አለኝ፦ ዓይንህን አቅንተህ እይ በበጎችና በፍየሎች ላይ የሚንጠላጠሉት የበጎችና የፍየሎች አውራዎች ሽመልመሌ መሰዮችና ዝንጕርጕሮች ነቁጣ ያለባቸውም ናቸው ላባ በአንተ ላይ የሚያደርገውን ሁሉ አይቼአለሁና።

ሐውልት የቀባህበት በዚያም **ለእኔ ስእለት የተሳልህበት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ** አሁንም ተነሥተህ ከዚህ አገር ውጣ፥ ወደ ተወለድህበትም ምድር ተመለስ።"

***የእግዚአብሔር መልአክ ለያዕቆብ በሕልም እንደ ተገለጠለትና ሳባ የሚያደርግበትን ግፍ እንደተመለከተ ከዚህ በኋላ ግን ዋጋውን የሚከፍለው እርሱ መሆኑን ይናገረውና ስለ ማንነቱ ሲናገር ግን ተናጋሪው መልአክ ሳይሆን በቤቴል የተገለጠለት ያህዌ የእርሱ አምላክ ስለትህን የተሳለለት መሆኑን በመረጃ ያቀርብለታል፡፡***

- **ዘጸ3፡2 እና የሐዋ7፡30-35 - *ለሙሴ***

እነዚህ ሁለት የምንባብ ክፍሎ በአንድነት በማጣመር መመልቱ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

"ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ።*የእግዚአብሔርም መልአክ* በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።"

"አርባ ዓመትም ሲሞላ *የጌታ መልአክ* በሲና ተራራ ምድረ በዳ በቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ታየው።ሙሴም አይቶ ባየው ተደነቀ፤ ሊመለከትም ሲቀርብ የጌታ ቃል። **እኔ የአባቶችህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ** ብሎ ወደ እርሱ መጣ። ሙሴም ተንቀጥቅጦ ሊመለከት አልደፈረም።ጌታም፡- የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች ምድር ናትና የእግርህን ጫማ አውልቅ።በግብፅ ያሉትን የሕዝቤን መከራ ፈጽሜ አይቼ መቃተታቸውንም ሰምቼ ላድናቸው ወረድሁ፤ አሁንም ና፥ ወደ ግብፅ እልክሃለሁ አለው።"

***በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ወይም የጌታ መልአክ መሆኑን ሁለቱም ይናገራሉ፤ ነገር ግን የሐዋርያት ሥራ ላይተገለጠው የአባቶች አምላክ እኔ ነኝ ብሎ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንደመጣ ያብራራልናል፡፡ በመሆኑም የተገለጠው መልአክ ሳይሆን ያህዌ ነው፡፡***

***በተመሳሳይ መልኩ በሚከተሉት የምንባብ ክፍሎ በእግዚአብሔር መልአክ አምሳያ እግዚአብሔር ወደ ሰዎች ልጆች ይገለጥ እንደ ነበር በብሉይ ኪዳን እንደ ማስረጃ ለምሳሌነት የሚጠቀሱ ክፍሎች ናቸው፡፡***

- ***መሳ*2፡1-4 - *ለእስራኤል ሕዝብ***
- ***መሳ*6፡11-24 - *ለጊዲዮን***
- ***መሳ*13፡3-23 - *ለሶምሶን ቤተሰብ***

- ***እንደ ሰው***

- **ዘፍ32፡24-32 እና *ሆሴ*12፡4 - *በያዕቆብ ሕይወት***

***እነዚህ ሁለት የምንባብ ክፍሎች ስለ አንድ ተመሳሳይ ታሪክ ይዘግባሉ፡፡ በመሆኑም ለተነሳንበት ክፍል እውነተኛ መረጃ ናቸው፡፡***

"ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር። እንዳላሸነፈውም ባየ ጊዜ የጭኑን ሹልዳ ነካው ያዕቆብም የጭኑ ሹልዳ ሲታገለው ደነዘዘ። እንዲህም አለው፡- ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ። እርሱም፡- ካልባረክኸኝ አልለቅቅህም አለው። እንዲህም አለው፡- ስምህ ማን ነው? እርሱም፡- ያዕቆብ ነኝ አለው።አለውም፡- ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና። ያዕቆብም። ስምህን ንገረኝ ብሎ ጠየቀው። እርሱም፡- ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? አለው። በዚያም ስፍራ ባረከው።ያዕቆብም። **እግዚአብሔርን ፊት ለፊት** አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው።"

"በማኅፀን ውስጥ ወንድሙን በተረከዙ ያዘው፥ በጕልማስነቱም ጊዜ **ከአምላክ ጋር ታገለ** ከመልአኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ አልቅሶም ለመነው። በቤቴልም አገኘው፥ በዚያም ከእኛ ጋር ተነጋገረ።እርሱም **የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው** የመታሰቢያው ስም እግዚአብሔር ነው።"

***ይህ ክፍል ያዕቆብ አንድ ሰው ሲታገለው እንዳደረ መናገር ይጀምራል ፤ በመቀጠልም ያሰው ይባርከዋል ያቆብም እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት በማለት ይደመድማል፡፡ የትንበተ ሆሴው ዘገባ ግን በግልጥ ከአምላክ ጋር ሲታገል ማደሩን እንዲያም "እኛ" በሚል የብዙ ቁጥር በመጠቀም ከገለጸ በኋላ የሰራዊት ሁሉ አምላክ መሆኑን በመግለጥ ይፈጽማል፡፡ እንግዲህ ለአብነት ያህል የምንመለከታቸው እንዚህ የምንባብ ክፍሎች እግዚአብሔር እራሱን ለሰዎች ልጆች የገለጠበትን መንገድ ለማስረዳት እንደ መረጃ ይጠቅሙናል፡፡***

- **ልዩ ግልጠት**
  - ኢያ5፡13-15 6:1-5

***አስቀድመን እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች እንደ መልአክ ደግሞም እንደ ሰው በመገለጥ የልቡን ሐሳብ ለመግለጥ እንዲሁም የሰዎችን ልጆች ከራሱ ሐሳብ ጋር ለማስማማት የተለጠበትን መንገዶች ስናይ ቆይተናል አሁን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በተለየ መንገድ እግዚአብሔር የተገለጠበትን ሁናቴ ከኢያሱ መጽሐፍ መመልከት እንችላለን፤***

"እንዲህም ሆነ፤ ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዓይኑን አንሥቶ ተመለከተ፥ እነሆም፥ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር፤ ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ። ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን? አለው። እርሱም፡- አይደለሁም፤ **እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ** ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ።

ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና። **ጌታዬ** ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው? አለው። **የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ** ኢያሱን። አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።

.... እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው። ተመልከት፥ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ጽኑዓን ኃያላንዋንም በእጅህ ሰጥቼአለሁ። ሰልፈኞቻችሁ ሁሉ ከተማይቱን አንድ ጊዜ ይዙሩአት እንዲሁም ስድስት ቀን አድርጉ። ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ በሰባተኛውም ቀን ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዙሩ፥ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ይንፉ። ቀንደ መለከቱም ባለማቋረጥ ሲነፋ፥ የመለከቱንም ድምፅ ስትሰሙ፥ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኹ የከተማይቱም ቅጥር ይወድቃል፥ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ይገባባታል።"

*እንግዲህ በዚህ ክፍል ልብ ብለን በኢያሱ እና ለኢያሱ ከተገለጠው አካል ጋር የተደረገውን ውይይት በጥሞና መመልከቱ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ በመጀመሪያ በኢያሪኮ ሜዳ ሳሉ የተገለጠው ሰው ነበር፡፡ አንተ ከማን ወገን ነህ ለሚለው ለኢያሱ ጥያቄ የሰውዬው መልሻ ግን እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ ነበር፡፡ ይህ እግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ በመሆን የተገለጠው የሚናገራቸው ሐሳቦች ግን የመለኮት ኃላፊነቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የእግርህን ጫማ አውልቅ የቆምክበት ሥፍራ የተቀደሰ በመሆኑ ምክንያት ማለቱ፤ ይህ ሐሳብ ሙሴ በቁጥቋጦ ውስጥ የተገለጠለትን ራዕይ ለመመለክት በቀረበ ጊዜ የሰማው የእግዚአብሔር አምላክ ድምጽ ነበር፤ ለኢያሱም እንደዚሁ ነው፡፡ ሐሳቡ ሲቀጥል በቀጥታ እግዚአብሔር መሆኑን በማያሻማ መልኩ "እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው" በማለት ቀጥሎ መደረግ ስላለበት የጉዞ ፕሮግራም መለኮታዊ መመሪያ ለኢያሱ ተሰጠው፡፡ አጭር እና ግልጥ ነው፤በኢያሪኮ ሜዳ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ በማለት እራሱን የገለጠው ሰው በንግግሩ እና በውይይቱ ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡*

*ማጠቃለያ፡- ከላይ በቀረቡት ማስረጃዊ የምንባብ ክፍሎች ውስጥ ማጤን ያለብን ጉዳይ*

1. *እግዚአብሔር እንደ መልአክ፣እንደ ሰው እና በልዩ ልዩ መንገድ ይገለጥ ነበር ብለናል፡፡ እነዚህ ከላይ ያነሳናቸውን የምንባብ ክፍሎች አውዳቸውን በምንመለከትበት ጊዜ ከአውዱ የምንወስደው ሀሳብ ትክክለኛ ፍቺ እንጂ ቃላቱን ብቻ መመልከት የትርጉም መዛባት እና የሐሳብ መፋለስን ያስከትላል፡፡ "መልአክ" የሚለውን ቦታ ሁሉ መልአክ ነው ብለን ከወሰድን እንሳሳታልን፡፡ ለምሳሌ፡- ራዕ*2:1 "በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤት ክርስቲያን <u>መልአክ</u> እንዲህ ብለህ ጻፍ።" *መልአክ የሚለውን ቃል በትክክልም መልዓክ ነው ብለን ከወሰድን ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ለማን ነው? በመሆኑም አውዳዊ የሆነ ፍቺ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት እጅጉን ጠቃሚ ነው፡፡*

2. የዚህን ሐሳብ መነሻ ለማስታወስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይገለጣል፤ ክርስቶስም የእግዚአብሔር መገለጫ መንገዱ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር እራሱን በብሉይ ኪዳን በክርስቶስ ይገልጥ ነበር፤ ክርስቶሰም እንደ መልዓክ ፤ እንደ ሰው እራሱን ለሰዎች ልጆች ይገለጥ እና ይታይ ነበር። ይህም መገለጡ ቲዮፋኒ ይባላል ነው ያልነው። ለአብነት ባየናቸው የምንባብ ክፍሎች ሁሉ እግዚአብሔር ነበር እንጂ ሰው አሊያም መልዓክ ነበር የተገለጠላቸው አላልንም በመሆኑም ይህ የተገለጠላቸው እራሱ ክርስቶስ ነበር።

### *ለ. ጥላ (አምሳያ)*

ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ እንደ ሰው እንደ መልአክ እና በሌሎችም በልዩ ልዩ መንገዶች እራሱን መግለጡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት እና መመልከት ይቻላል። ነገር ግን ደግሞ በቀደመው ኪዳን ታሪክ ዘገባ ውስጥ የክርስቶስን እውነተኛውን አካል በአምሳያነት ወይም በምሳሌነት ሲያገለግሉ የነበሩ ሐሳቦችም ተዘርዝረዋል። እውተኛው አካል የመጣው በ6 ወይም በ5 ዓ.ዓ ላይ ነው። ነገር ግን ይህን ወደፊት ሊሆን ያለውን የክርስቶስን መገለጥ፣ ዓላማውን፣ ተግባሩን እና መንገዱን ለሰዎች ልጆች ግልጥ ለማድረግ እግዚአብሔር አስቀድሞ በምሳሌ አስረድቶአል። እነዚህምን መንገዶች የክርስቶስ የእውነተኛው መገለጥ ጥላ ወይም አምሳያ ብለን እንጠራቸዋለን። ከእነዚህም መካከል

- ✓ ሮሜ5፡14 - አዳም

" ነገር ግን በአዳም መተላለፍ <u>ምሳሌ</u> ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ *አምሳት* ነውና።"

አዳም ኃጢያትን በመስራቱ ምክንያት ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ። በአንዱ አዳም ምክንያት ኃጢያት ለሰው ሁሉ ደረሰ።በተመሳሳይ መልኩ በአንዱ በክርስቶስ ምክንያት ሕይወት ደግሞ ለሰው ሁሉ ደረሰ። ይህ ጉዳይ ኃጢያት በሥጋ ከወለዱን ከአባቶቻችን (ከወላጆቻችን) እንደማይደርን ይነግረናል።በተመሳሳይ መልኩ ጽድቅንም ወይም ሕይወትንም አማኝ ከሆኑ ወላጆቻችን አናገኝም ከአንዱ ከክርስቶስ ሁሉም በራሱ በግሉ ይቀበላል እንጂ የቀደመው አዳም ለዚህ ጉዳይ አምሳያ እና ጥላ ነበር።

- ✓ ቆላ2፡17 - ብሉይ ከዳናዊ በዓላት

"እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ።እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች <u>ጥላ</u> ናቸውና፥ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።"

ጳውሎስ በመልዕክቱ ለቆላስይስ ሰዎች በሚበላ በሚጠጣ እና ስለ ልዩ ልዩ ብሉይ ኪዳናዊ በዓለት ላይ ተመስርቶ ስለምን ይህን አታደርጉም ብሎ ፍርድን ሊሰጣችሁ አይገባም ይላል ፤ ምክንያቱን ደግሞ ሲያብራራ እነዚህ ጉዳዮች መልክታቸውን አስተላልፈው ጨርሰዋል። ሊመጣ ያለውን ክርስቶስን

**ለማስረዳት ነበር የቆሙት አሁን ግን የሚናገሩለት ጉዳይ እራሱ ስለመጣ ተግባራቸውን ፈጽመዋል የሚል ምክንያትን ይሰጣል።በተጨማሪነት ልብ በለን ልንመለከታቸው የሚገቡ የፋሲካ በዓል - 1ቆሮ5፡7**

**የቂጣ በዓል፣ የማስተሰሪያ ቀን በዓል - ዘሌ16፡15-22፤ሮሜ3፡25፤ዕብ9፡7-8፤23-28 ፣ የበኩራት በዓል - 1ቆሮ15፡20-23 ፣ዳስ በዓል - ዘካ14፡16-19 ናቸው።**

| ተ.ቁ | በዓላት | የሚከበርበት ቀን | ዓላማው |
|---|---|---|---|
| 1 | ሰንበት | በሰባተኛው ቀን | እግዚአብሐር ፍጥረትን ከፈጠረ በኋላ እንዳረፈ ለማሰብ |
| 2 | ፋሲካ | በመጀመሪያው/አቢብ/ ወር በ17ኛው ቀን /በእኛ ሚያዝያ/ | ከግብጽ ባርነት ቤት የመውጣት መታሰቢያ በዓል ሲሆን ከሞት መላዕክ የበሩ መቃን ላይ በተቀባው ደም ስለመዳናቸው ለመዘከር |
| 3 | የቂጣ በዓል | በ15ኛው ቀን ከፋሲካ በዓል ቀጥሎ ለ7 ተከታታይ ቀናት | እስራኤላዊያን ከግብጽ እንዴት እንደ ወጡ አወጣጣቸውን ለማሰብ |
| 4 | የበኩራት | የመጀመሪያው ምርት ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ነው | የመከር ወር በኩራትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ |
| 5 | በዓለሃምሳ | ከመከር ከ50 ቀናት በኋላ በ3ኛው ወር በሲዋን ወር /በእኛ ሰኔ/ | ስለ ተሰበሰበው መከር እግዚአብሔርን ለማመስገን እና በፊቱም ደስ ለመሰኘት |
| 6 | የመለከት | በሰባተኛው ወር /አታኒም/ በምድሪቱ ሁሉ ለአንድ ቀን መለከት በመንፋት በእኛ ጥቅምት | የመከራ ወራት ተጠናቆ አደስ ወራት እንደ ተጀመረ ለማብስር ነው። (መስከረም ጠባ እንደ ማለት ነው) |
| 7 | የማስተሰሪያ | በሰባተኛው ወር /አታኒም/ ጥቅምት | ካህናቱ የሕዝቡን ኃጢያት የሚያስተሰርዩበት እና በጾም በጸሎት የሚከናወን በዓል ነው፤ |
| 8 | የዳስ | በሰባተኛው ወር በ15ኛው ቀን | እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ካወጣ በኋላ በምድረ በዳ እንደ መራቸው ጉዞቸውን ለማሰብ ነው፤ |
| 9 | የ7ኛው ዓመት | ከስድስተኛው ዓመት በኋላ | ስድስት ዓመት ከዘሩ በኋላ 7ኛው ዓመት ምድሪቱ አትታረስም ታርፋለች |
| 10 | የኢዩቤልዩ ዓመት | 7X 7ዓመታት በኋላ በ7ኛው ወር በ10ኛው ቀን | በምድሪቱ ላሉ ነዋሪዎች ሁሉ የነጻነት አዋጅ |

✓ ዕብ10፡1 - የመቅደስ ሥርዓተ ሕጉ እና መሰዋዕቶች

"ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም።"

ለኃጢያት መንጻት እንዲሆኑ የተደነገጉ ሕጎች በሙሉ ሰውን ከኃጢያቱ እና ከበደሉ ሁሉ ፈጽሞ ያነጹታል ማለት ሳይሆን እነዚህ ነገሮች ሰዎች እውነተኛ አካሉ የሆነው ክርስቶስ ሲመጣ እንዴት ሰው ከበደሉ እና ከኃጢያቱ መንፃት እንደሚችል ምሳሌያዊ ገለጣዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ክርስቶስ በልዩ ልዩ መሰዋዕቶች መንጻት የማይቻለውን የስን ኃጢያት በገዛ ደሙ እንደቀሰ እና እንዳነጸ አመላካች ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ የምስዋእት ዓይነቶች የሚቃጠል መሰዋዕት -ዘጸ29፡15-18፣ የእህል መስዋዕት ፣ የደህንነት መስዋዕት- ሌዋ3፡6-11፣ የኃጢያት መሰዋዕት - ዘጸ29፡10-14፣ የበደል መሰዋዕት- ሌዋ5፡1-7፣

| ተ.ቁ | የመሠዋዕቱ ዓይነት | የመስዋዕቱ ምንነት | ዓላማው |
|---|---|---|---|
| 1 | የሚቃጠል 1፡1-17 | በመሰዊያው ላይ በሙሉ የሚቃጠል የሰርክ መስዋዕት /ዘወትር በየቀኑ የመቀርብ/ | ኃጢያተኛ ሰው ለኃጢያት ይቅርታው በፈቃደኝት የሚያቀርበው |
| 2 | የእህል ቁርባን 2፤ 6፡14-23 | ደስ የሚያሰኝ መዓዛ ማር ወይም እርሾ የሌለበት መስዋዕት | ለእግዚአብሔር አክብሮትንና ምስጋናን ለመግለጽ |
| 3 | የህብረት መስዋዕት 3 ፤ 7፡11-34 | በእግዚአብሔር እና በምሥዋዕት አቅራቢው መካከል ህብረትን ለመግለጽ | ለእግዚአብሔር ምስጋና እና አምልኮ ማቅረብን ለመግለጽ |
| 4 | የኃጢያት መሰዋዕት 4፡1-5፡13፤6፡24-30 | ባለማወቅ ስለተፈጸመ ኃጢያት ለማስተሰረይ እና ለመንጻት | የኃጢያት ይቅርታን መቀበል |
| 5 | የበደል/የመተላለፍ መስዋዕት 5፡14 -6፡7 7፡1-6 | በእግዚአብሔርና በሰዎች ላይ ስለ ተፈጸመው ኃጢያት ለማስተሰረይ በሰው ላይ ስለተፈጸለመው በደል ማስተሰሪያ 20 በሙቶ ካሳ ክፍያ፤ | የካሳ ክፍያ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው |

- ✓ ዕብ8፡1-7፤10፡11-14 - አምሳያ የነበሩ ሥርዓቶች

የቀደመው ኪዳን የመቅደስ አገልግሎት እና የሊቀ ክህነት ሥርዓቱ በሙሉ ስለ አካሉ የወደፊት አገልግሎት አስፈላጊነት ለማሳየት እንደ ጥላ ሆነው አገልግለዋል፡፡ አሮን ለሊቀ ክህነት አገልግሎት ፋና ወጊ ነው፤ በመሆኑም ስለ ሊቀ ክንነት ማውሳት እና አስፈላጊነቱን መረዳት የሚቻለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ክርስቶስ ግን እውነተኛው ሊቀ ካህን በእውነተኛው የአገልግሎት ድንኳን የገዛ ደሙን በማያዝ ለራሱ ሳይሆን ለሰዎች ልጆች በደልና ኃጢያት የሚሆንን የገዛ ደሙን ይዞ ገባ፡፡

- ✓ 1ጴጥ3፡21 አምሳያ የነበሩ ሁኔታዎች

በኖህ መርከብ የዳኑ ሰዎች ለዛሬው በክርስቶስ ሞትን እና ትንሣኤ አምኖ ለመዳን እንደጥላ ሆኖ ነው ያገለገለን፡፡ በመሆኑም የኖኅ መርከብ በቀደመው ኪዳን ውስጥ እንደ ሆኖ ነው ያገለገለን፡፡

- ✓ ዮሐ3፡14-16 - አምሳያ የነበሩ ነገሮች

በምድረበዳ የተሰቀለው የንሐስ እባብ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረማቸው ምክንያት የሚናደፍን እባብ ሰድዶባቸው ነበር፡፡ዘኁ21፡4-5 "ከሖርም ተራራ ከኤዶምያስ ምድር ርቀው ሊዞሩ በኤርትራ ባሕር መንገድ ተጓዙ የሕዝቡም ሰውነት ከመንገዱ የተነሣ ደከመ፡፡ሕዝቡም በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ፡፡ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም፥ ውኃ የለም ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ ብለው ተናገሩ፡፡እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ፥ ሕዝቡንም ነደፉ ከእስራኤልም ብዙ ሰዎች ሞቱ፡፡" በዚህ ሳቢያ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጸለያ ጌታም የንሐስ እባብ ሰርቶ እንዲሰቅል እና ወደ እርሱ የሚመለከት ሁሉ እንደሚድን ተናገረው፡፡ ይህን ምሳሌ ጌታ ከኒቆዲሞስ ጋር በነበረው ውይይት የሰው ልጅ ልክ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባወል አለ፡፡

### *ሐ. ትንቢታዊ ንግርቱ*

ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የታሪክ ዘገባ ውስጥ እንዴት እንደቀረበ ከምንመለከተበት ክፍል ይህ የመጨረሻ ነው በትምህርታችን፡፡ በመሆኑም ስለ ክርስቶስ አጠቃላይ ሁኔታ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ምንም በማያሻማ መልኩ ቀርቦአል፡፡ከእነዚህም መካከል ለአብነት ያህል የምንመለከታቸው የሚከተሉቱን ነው፡፡

1. ሰው ሥለመሆኑ የተነገሩ - ክርስቶስ ሰው እንደሚሆን እና የሰዎችን ልጆች እውነተኛ ባርኮት እንደሚመልስ የተነገረበት ክፍሎች ናቸው፡፡

   - ዘፍ 3፡15 "በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ፡፡"

- ❖ ዘፍ12፡1-3 "…የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፡፡" (ለአብርሃም)
- ❖ ዘፍ25፡4 "…የምድርም አህዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፡፡" (ለይስሐቅ)
- ❖ ዘፍ28፡14 "…የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተ በዘርህም ይባረካሉ፡፡" (ለያዕቆብ)

2. ስለ ልደቱ (ስለ መወለዱ) የተነገሩ - አዲሱ ኪዳን በወንጌላት ስለ አወላዱ የዘገው ታሪክ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በብሉዩ ከዳን ስለ ልደቱ የተዘገቡ ክፍሎች ናቸው፡፡

   - ሚክ5፡2 "አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡"
   - ኢሳ7፡14 "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡፡"

3. ስለ ምድራዊ ሕይወቱ እና አገልግሎቱ - ወደ ፊት በሚኖረው አገልግሎት ዙሪያ የተነገሩ ንግሮች እጅግ አስገራሚ ናቸው፡፡

   - ሚል3፡1 "…እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል የምትወዱትም የቃል ኪዳን *መልእክተኛ* እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦"
   - ዘዳ18፡15-18 "…አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ *ነቢይ* ያስነሣልሃል እርሱንም ታደምጣለህ፡፡"
   - ኢሳ61፡1-2 "የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች *የምሥራችን እሰብክ* ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል፡፡ የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፥ በአመድ ፋንታ አክሊልን፥ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፥ በኀዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል፡፡"

4. ስለ መከራው እና ሞቱ - ስለ መከራው እና ሞቱ ከተነገሩት አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካካል እን ኢሳ53 የሚያክል የለም! እጅግ በሚገርም ሁኔታ ስለ ክርስቶስ ሕመሙ እና ስቃዩ የእግዚአብሔር አምላክም ሐሳብ ምን እንደሆነ በግልጥ የተናገር የትንቢት ክፍል ነው፡፡ በአንዳንድ ስዎች ዘንድም እንደ ወንጌል ክፍል ተደርጎ የሚቆጠር ነው፡፡

- መዝ 22 " አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?... እንደ ውኃ ፈሰስሁ አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ ልቤ እንደ ሰም ሆነ፥ በአንጀቴም መካከል ቀለጠ።ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ፥ በጕሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ፥ ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ።ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።"
- ኢሳ53 በሙሉ ዘወትር ሊነበብ እና ሊጠና የሚገባው ክፍል ነው።

5. ስለ ትንሳዔው እና ሙከብሩ

- መዝ 16፡10 "ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።"
- ዳን7፡14 "በሌሊት ራእይ አየሁ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት።ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።"

6. በአብ ቀኝ ስለመቀመጡ - ጌታ የድነትን ሥራ በመስቀል ከፈፀመ በኋላ ከሥራው እንዳረፈ የሚገለጥ ሐሳብ አስቀድሞ የተነገረው ሐሳብ ያለው በቀደመው ኪዳን ውስጥ መሆኑን አመላካች ነው።

- መዝ110፡1 "እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።"

7. ክርስቶስ የሊቀ ክህነትን ማዕረግ ስለ መቀበሉ - መዝ110፡4- "እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም።"

በአርግጥ የሊቀ ክህንነት ተግባር እና ኃላፊነት ምን እንደሆነ በውል መረዳት የክርስቶስን የሊቀ ክህነት አስፈላጊነት እንድንገነዘብ ያስችለናል። በመሆኑም ሊቀ ካህናት ከሰው መካከል ስለ ሰው በእግዚብሔር ፊት የሚቆሙ ናቸው። ስለዚህም ምክንያት ልብ ሊባሉ የሚገቡ ነጥቦች አሉ

1ኛ/ ሊቀ ካህን ሰው መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ስለ ሰው ድካም በእግዚብሔር ፊት ለማቅረብ ሰዎችን የሚረዳ መሆኑ ዋና ጉዳይ ነው።

2ኛ/ ሊቀ ክህነት ማዕረግ ሲሆን - ሹመቱም የሚሰጠው ከሰው ዘንድ አይደለም ልክ እንደ አሮን የትኛውም ሊቀ ካህን የሹመቱ ምንጭ እራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

3ኛ/ ተግባሩ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከለ መካከለኛ/አማላጅ መሆን ነው። ይህ ጉዳይ ሁለት ነገሮችን ያካትታል የመጀመሪያው ስለ ሰው ልጆች ኃጢያት የበደል ስርየትን

ማቅረብ ሲሆን ሊቀ ካህኑ አሮንም ይህንን ለመፈጸም በአመት አንድ ጊዜ ስለ ራሱ እና ስለ ሕዝቡ የሚሆንን የደም መሥዋዕት ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ይገባ ነበር፡፡ ክርስቶስም ለራሱ ሳይን ስለ ሰው ልጆች ሁሉ የሚሆንን የኃጢያት ማስተሰርያ የሚሆንን የገዛ ደሙን ይዞ ወደ እውተኛይቱ ድንኳን ገባ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሕዝቡ እና እግዚአብሔር መካከል በሚፈጠር በደል መቅሰፍት ሲነሣ በመካከል በመግባት ሕዝቡና እግዚአብሔርን ማስታረቅ ነው (ይኸውም መታየት ወይም መማለድ) ነው፡፡ ለዚህም ሐሳብ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት ዘኁ16፡41-50 ያለውን ክፍል ይመልከቱ፡፡ በመሆኑም ክርስቶስ ዛሬም ስለ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት ይታይላቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ነው የክርስቶስ አማላጅነት የሚጀመረው፡፡ ልብ በሉ ማንም በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሳቢያ ሊቀ ክህነትን ካለተቀበለ በቀር አማላጅ/መካከለኛ/ጠበቃ መሆን አይችልም፡፡ ስለ ሰዎች በጸሎት መቃተትን መለመንን እንደ አማላጅነት መውሰድ የእኛ የአማርኛ አገባብ እና ትርጉም እንጂ አማላጅነትን ከክርስቶስ አንጻር ስናነሳ መለመን ሳይሆን መታየት ነው፡፡ ደግሞም አማላጅነት ከሊቀ ክህነት ተነጥሎ የሚታይም ወይም የሚታሰብም አይደለም፡፡ በመሆኑም አማላጅነት ጠበቃ መሆን ነው፡፡ማዕርግ ነው፡፡ሹመት ነው፡፡

# 4. ተሰግዖ - ቃል ሥጋ/ሰው የመሆኑ ሚስጥር

ከቅድመ ዘለዓለም የነበረው ቃል (ሎጎስ) በሚል ስያሜ ክብር የነበረው ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር ብቸኛ መገለጫ እንደነበር እና በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ እንደ ተሰው እንደ መልዓክ ሲገለጥ ነበር፡፡ አሁን ግን ይህ ቃል ወይም "ሎጎስ" ሰው ሆነ! በእርግጥ ይህ ሐሳብ በጣም ትልቅ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ሐሳብ ነው፤ ምክንያቱም በቃላት እና በሐሳብ አገላለጽ ግድፈት ሳቢያ ትልቅ ስህተት ይከሰታልና፡፡ በመሆኑም በቀደሙት አባቶች ዘንድ በሀገራችን ሆነ ከአገር ውጭ ባሉ ሊቃውንት እጅግ ብዙ የተባለለት ነው፡፡

**የቃሉ ፍቺ - ተሰግዖ**

"ተሠግዎ" የሚለው ቃል በተለምዶ ጥቅም ላይ የሚውለው እግዚአብሔር የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው እንደ ሆነ ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም፤ ነገር ግን የመጣው ከላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም "በሥጋ ውስጥ" ማለት ነው፡፡ ከኢየሱስ ጋር በተገናኘ መልኩ ግን ቃል ወይም ሎጎስ የሰውን መልክ ይዞ ሰው መሆኑን እና መገለጡን ያስረዳል (ዮሐ1፡14፤1ጢሞ3፡16)

አቶ በልሁ ደለለኝ በመጽሐፋቸው የቃላት ፊቺ ላይ የገለፁት - ትሥጉት (Incarnation) የአካላዊ ቃል ሥጋ መሆንን የሚያመለክትና "ቃልም ሥጋ ሆነ…" የሚለው ጥቅስ አጠራር ነው፤ በማለት አስቀምጠዋል፡፡

***አቶ መሰረት ስብሐት ለአብ ስማ ጽድቅ ብሔራዊ በተሰኘው መጽሐፋቸው ስለ ተሰግዖ የሰጡት ትርጓሜ ደግሞ እንደዚህ ይላል "እኛ ግን እንደ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ትርጓሜ " አምላክ ሰው ሆነ " ማለትን የሰውን ህላዌ ወሰደ ተቀበለ ተገነዘበ የራሱ አደረገ (ሉቃ1፡35፤ፊል2፡7፤ 1ጢሞ2፡5) በማለት እናምናለን፡፡ይህንም ስላልን "አምላክ በቅዱሳኑ እንደሚያድር ልክ በትስብእቱ አደረ" ማለታችን አይደለም፡፡ቃል ራሱ ሳይጠፋና ሳይለወጥ የሰውን አካል የራሱን አካል አደረገ፡፡" በማለት አስቀምጠውታል፡፡***

***በመሆኑም ቃል ስጋ ሆነ የሚለው የሐዋርያው ዮሐንስ አገላለጽ በሁላችንም ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ ብለን እንድናስብና እንድናምን ያደርገናል፡፡***(ዮሐ1፡14)

***ይሁን እንጂ ይህንን ሐሳብ የበለጠ ለመረዳት ከመጀመራችን በፊት ልብ ልንላቸው የሚገቡ የምንባብ ክፍሎች አሉ፡፡ በተለይም ደግሞ ሉቃ***1፡31-35 ***እና ዕብ*** 2፡14-18 ***ያለውን ክፍል፡፡***

1ኛ/ ***ሉቃ***1፡31-35

> "እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።ማርያምም መልአኩን። ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፦ *መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል* ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።ማርያምም። እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ።"

➔***ይህን የምንባብ ክፍል "ኢየሱስ ክርስቶስ አዳማዊውን ኃጢያት ከማሪያም ከእናቱ ላለመውሰዱ የልዑል ኃይል ስለ ጸለለላት ነው" ብሎ ማለት ይቻላል? በእርግጥ ሐሳቡን ወይም ጥያቄውን ከዚህ የምንባብ ክፍል ጋር ሳያገናኙ ማንሳቱ ለሥነ-ክርስቶስ ጥናት ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ የምንባብ ክፍል መሠረታዊ ሐሳብ መልዓኩ ለማሪያም ስላበሰራት የምስራች ከወንድ ጋር ውሲባዊ ሕብረት ሳይኖረኝ እንዴት ልወልድ ወይም ልጸንስ እችላለሁ ብላ ለጠየቀችው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ነው፡፡ ምላሹም ፡-***

***ሀ. መንፈስ ቅዱሱ በአንቺ ላይ ይመጣል፤***

***ለ. የልዑል ኃይል ይጸልልሻል ፤ (ስለዚህ…ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል)***

***ሐ. ዘመድሽ ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወራት ከጸነሰች እነሆ ሶስት ወርዋ ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና የሚል ነው፡፡***

በዚህ ውስጥ "መጸለል" ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ሊፈታ የሚገበው ጥያቄ ነው። ምክንያቱም "መጽለል" መጋረድ ነው ከሚለው ጽንሰ ሐሳብ በመነሳት የልዑል ኃይል የጋረደው ኃጢያትን ነው የሚል ደምዳሜ ላይ ስለሚደረስ። አስቀድመን እንዳልነው ይህንን የመሰለ ትርጓሜ ለመስጠት አውዱ አይደግፈንም፤ አውዱ የምስራች ተበሰረ፣ ይህ የምስራች እንዴት ይሆናል የሚል ጥያቄን አስነሳ ፤ ለቀረበው ጥያቂ ተገቢ ማስረጃ አዘል ምላሽ ተሠጠ። በታሪኩ ውስጥ የተሳተፉት ማሪያም እና መልዓኩ የሚያስቡት እና የሚናጋገሩት ሐቅ ነው የአውዱ ገዢ ሐሳብ። በእርግጥ "መጽለል" የሚለው ቃል ትርጓሜ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ማየት እጅጉን ጠቃሚ ነው።

- ሕያው ቃል "..የእግዚአብሔርም ኃይል <u>ይጋርድሻል</u>።" ፣
- መጽሐፍ ቅዱስ ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1997 "የልዑል እግዚአብሔርም ኃይል <u>በአንቺ ላይ ይሆናል፤"</u> ፣
- በወጪው ቋንቋ "The Holy Spirit will come upon you, the power of the Highest <u>hover over you</u>;" ፣
- "The Holy Spirit will come on you, and the power of the Most High will <u>come to rest on you</u>,"
- በአፋን ኦሮሞ "Hafuurri qulqulluun siirra in bu'a, humni aabaas <u>si golbooba</u>,"

ከእነዚህ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች መረዳት የሚቻለው - "የጸልልሻል"፣ "ይጋርድሻል" ፣ "በአንቺ ላይ ይሆናል" ፣ "በአንቺ ላይ ይሰፍፋል" ፣ "በአንቺ ላይ ያርፋል" እና "ይከብብሻል" የሚል ጸንሰ ሐሳብ የያዘ ነው። በእርግጥ እነዚህ ሁሉ ቃላት በተለያየ መንገድ የሚናገሩት ማሪያም ልጅ እንዴት መውለድ እንደምትችል ማስገንዘቢያ ናቸው። በመሆኑም የኢየሱስ ክርስቶስን አዳማዊ ኃጢያት አልቦነት ለማስረዳት ይህንን ጥቅስ መጠቀሙ አቅም ያለው አይሆንም።

2ኛ/ ዕብ 2:14-18

> "እንግዲህ ልጆቹ <u>በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥</u> እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ <u>በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ</u>። <u>*የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም*</u። ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ <u>በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው</u>። እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።"

በዚህ የምንባብ ክፍል ላይ ተመስርቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማሪያም የዘር ክፋይ ተካፋይ ነው። ማለት ይቻላል? አስቀድሞ በተመለክትነው የምንባብ ክፍል ላይ እንዳልነው በተመሳሳይ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማሪያም ዘር ክፋይ ተካፋይ ነው ወይስ አይደለም? በሌላ አገላለጥ ጌታችን ከማሪያም ስጋ ነስቶአል አልነሳም ?ብሎ ከዚህ የምንባብ ክፍል ጋር ሳያያዙ ጥያቄውን ማንሳት እጅግ ተገቢ ነው ለሥነ-ክርስቶስ ጥናት። የዚህ የምንባብ ክፍል መሰረታዊ ሐሳብ ግን ሁላችንም ልብ እንደምንለው የዕብራዊያኑ ጸሐፊ በምዕራፍ አንድ ላይ እግዚአብሔር በመጨረሻ ዘመን በአንዱ ልጁ ተናገር ይላል። ለዚህ ንግግር ሰዎች ተገቢ የሆነ ምላሽ መስጠት እንዳላበቸው ለማብራራ የምልዕክቱን ትልቅነት ያስረዳል። አስቀድሞ በነበረው ኪዳን በመላዕክት መካከለኝነት የተነገረውን የእግዚአብሔርን ንግግር የተላለፈ እና ችላ ያለ ሰው ትልቅ ቅጣት ከተቀበለ በልጁ የተነገረውን ቃል የሚተላለፍ የሚብስ ቅጣት እንደሚጠብቀው ለማብራራት የልጁ ከመላዕክት በላይ መሆን በምዕራፍ አንድ እና ሁለት ይገልጻል።

በዚህ መሐል በምንባብ ክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ዕብ1:2 ፣ አምላክ የሆነ ዕብ1:8 ፣ ወንድሞችን በውርደቱ ከፍ ለማድረግ ወንድሞችን መሰለ ዕብ2:10፤14 በማለት ከገለጸ በኋላ ስለምን ወንድሞቹን መምሰል እንዳለበት ያስረዳል። በመሆኑም ይህ ክፍል ክርስቶስ እንዴት ሰው እንደሆነ ሳይሆን ስለምን ሰው እንደሆነ ለማስረዳት የተነሳ የምንባብ ክፍል ነው። ይህንን ለመረዳት

ሀ. ወንድሞቹን መምሰል የተገባው - በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ለመሻር ፤

ለ. በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በሞት ፍርሃት ተገዝተው ያሉትን ሰዎች ነጻ ለማውጣት፤

ሐ. የአብርሃም ዘር የሆኑት ወገኖች ለመርዳት ፤

መ. የሕዝብን ኃጢያት ለማስተሰረይ፣ የሚምር እና የታመነ ሊቀ ካህናት ለመሆን ሰው ሆነ። በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ሂደት ውስጥ ሁል ጊዜ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ አውዱ ነው። በዚህ የምንባብ ክፍል በጸሐፊው እና በተቀባዮቹ ማካከል ስለነበረው የሐሳብ ግንኙነት መረዳት ደግሞ ይበልጥ አንድን የምንባብ ክፍል ለመረዳት እጅጉን ይጠቅማል። ይህን አሁን እኔ ማስበውን ነው የመልዕክቱ ተደራሲያን (ተቀባዮች) የሚረዱት በሌላ አነጋገር ለመጀመሪያ ተቀባዮቹ ሊናገር ያልቻለውን ነገር ለእኛ ሊናገር ስለማይችል ማለት ነው።

በተለይ ደግሞ ቁጥር 16ን በተለየ መልኩ መመልከት አስፈላጊ ነው።የዚህ ምክንያት ደግሞ በተልምደ የተገኘውን ትርጉም ስለምንከተል እና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን ያላጤነ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የምንጠቀመው መደበኛው የ1954 ዓ.ም እትም በመሆኑ ከአማርኛ የሰዋስዎ አገባብ እና የቃላት ክብደት ለአረዳድ ክፍተት ፈጣሪ ይሆንብናል። “የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።” አስቀድመን እንዳልነው ሁሉ የዚህ የምንባብ ክፍ ገዢው ሐሳብ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለምን ሰው እንደሆነ ነው። በመሆኑም ሰው የሆነበት ምክንያት የአብርሃምን ዘር ለመርዳት ወይም ለማገዝ ነው። እስቲ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን እንመልከት

- NKJV

  16 "For indeed He does not give **aid to angels**, but He does give **aid to the seed of Abraham.**"
- ASV

  16 "For verily **not to angels doth he give help**, but he **giveth help to the seed of Abraham.**"
- ሕያው ቃል

  "አመጣጡም የአብርሃምን ዘሮች ለመርዳት እንጂ  መላእክትን ለመርዳት አይደለም፡፡"
- በ1980 ዓ.ም እትም (መጽሐፍ ቅዱስ ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ)

  "ምክንያቱም የኢየሱስ ፍላጎት  መላዕክትን ለመርዳት ሳይሆን የአብርሃም ዘር ለመርዳት አስቦ ነው፡፡ ስለዚህ በሁሉ ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው…"
- አፋን ኦሮሞ

  "Inno ergamootaaf utuu hin ta'in, sanyii Abrahaamiif in dhimma."

ከእነዚህ ልዩ ልዩ ትርጉሞች የተገኙት አገላለጦት የምንባብ ክፍሉን በውል ለመረዳት እንድንችል እንደሚረዱ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ያስፈለገው ሰዎችን ለመርዳት ነው ፣ መላዕክት ለመርዳት አይደለም፡፡ ከሰው ልጆች አስቀድሞ የተፈጠሩትም መላዕክት ናቸው ፤ ስህተት እና ውድቀትም የጀመረው ከሰው አስቀድሞ በእነርሱ መካካል ነው፡፡ ጌታ ግን የወደቀውን የሰዎችን ልጆች ለመረዳት ሰው ሆነ፣ እኛን መሰለ ይለናል፡፡

ማጠቃለያ፡- በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ጌታችን የሰው ዘር እንደሆነ ለማስረዳት የተጠቀሱ ሐሳቦች አሉ፡፡ በእርግጥም የሰው ዘር ነው፡፡ አሁንም ግን አውዳዊ ፍቺያቸውን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ "ዘር" የሚለው ቃል ሁሉ እኛ በልባችን የምናሰብውን ነው የሚገልጠው ብሎ ማለት ግን ተገቢ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት አይሆንም፡፡

➔ማቴዎስ በወንጌሉ መግቢያ ላይ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ ማለት ክርስቶስ እንደተስፋው ቃል መወለዱን እና የአብርሃም ዘር መሆኑን ለአይሁዳዊያኑ አውድ ሊገባቸው በሚችል ሐሳብ ግልጥ አድርጎአል፡፡ (1፡1-17) በዚህ የዮሴፍን የዘርግ ሐርግ ተከትሎ ነው ያለቀው ዘገባው ምክንያቱም ዩሴፍ ለጌታችን የሕግ አባቱ ነው፡፡

➔ሉቃስ ደግሞ ለአሕዛቡ ለቴዎፍሎስ እንደመጻፉ መጠን ክርስቶስን የአዳም ዘር እንደሆነ ነው ያቀረበው በመሆኑም ከዮሴፍ ተነስቶ ሽቅብ ወደ ላይ ወይም ወደ ኋላ በመቁጥር አዳም ዘንድ ደርሶ በመስተጨረሻም የእግዚአብሔር ልጅ በማለት ይደመድማል፡፡ (3፡23-38)

**ቃል ሥጋ በመሆኑ ሂደት ያሉ ሁለት አመለካከቶች**

ከላይ የዘረዘርናቸው ሐሳቦች እንደ ተጠበቁ ሆነው፤ የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆንን አስመልክቶ እንዴት ሰው እንደሆነ ለመግለጥ በግልጥ የሚታወቁ ሁለት አመለካከቶች አሉ፡፡

- የመጀመሪያው፡-
  - ❖ ከማርያም ሥጋ ተካፍሏል/ነስቷል

ኢየሱስ ሰው ለመሆን የሚያስችለውን ነገር ከማርያም ዘርን በመውሰድ ከሰው ሥጋና ደምን ተካፍሎአል፡፡ በመሆኑም ትክክለኛ ሰው ለመሆን ችሎአል፡፡

- ሁለተኛው፡-
  - ❖ ከማርያም ሥጋ አልተካፈለም

ኢየሱስ ሰው ለመሆን ከማርያም ዘርን መውሰድ አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም ከወንድ ዘርን እንዳልወሰደ ሁሉ ከሴቲቱ እንዲሁ አልወሰደም፤ ነገር ግን ሰው ሆኖ እንዲወለድ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ዋነኛው ነው፡፡

**ማሳሰቢያ**፡- በሁለቱም አቅጣጫ ባሉት አመለካከቶች ዘንድ ለብዙ ዘመናት በቀደሙት አባቶች እና በቤተ እምነቶች መካከል እንዲሁም በአማኞች መካከል ብዙ ክርክር እና ወይይቶች ተደርገዋል እየተደረጉም አሉ ወደ አንድ አመለካከት መምጣት ግን እስከ አሁን አልተቻለም፤ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ኢየሱስ ሰው መሆኑን በውል መረዳቱ ነው፡፡ ክርስቶስ ሰው የሚመስል ፣ የሰው ምሳሌ አሊያም ሌላ አይደለም ግን ክርስቶስ ሰው ነው፡፡

# 5. የክርስቶስ ማንነት

## ሀ. ክርስቶስ ማነው?

በዚህ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባ ቁልፍ ሃሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም የብዙ ቤተ እምነቶች አለመግባባት አለመስማማት የስህተት ትመህርቶችም ቅርጽ እና ቁጥር መብዛት ይህ የክርስቶስ ማንነት ላይ ያለን የመረዳት ችግር ነው፡፡ነገር ግን እንደ መጻሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ሐሳብ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትን ፍጹም ሰው እንዲሁም ፍጹም ዓምላክ□እንደሆነ ያመለክትል፡፡

**አ□ም ሰዉ ነው**

የክርስቶስን ሰው መሆን ብንቀበልም እንኳን *«አ□ም ሰዉ»* ነው የሚለውን ዓረፍተ ነገር በሚገባ መረዳት ይገባል፡፡በቃል ደረጃ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡

<u>በመጀመሪያ ሙሉ በሙሉ ሰው ነው።</u> ሙሉ በሙሉ ማለት ሰው አይደለም የሚያሰኝ ምንም ነገር የለውም፣አልያም መቶ በመቶ ያለምንም ነጥብ ጉደለት በእኛ ቋንቋ ሰውን ሰው ነው ሊጸስብለዉ የሚችል ነገሮችን ያሟላ ሰው ነው ማለት ሲሆን።

<u>በሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ሀጢያት የለሽ ነው ለማለት ነው</u>። ይህም አባባል የአዳማዊ የሀጢየት ባህርይ ሆነ የድርጊት ኃጢያት በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ምንም ስፍራ የላቸውም፣ስለዚህ ከቅዱስና እና ከኃጢያት አንጻር ምንም እንከን የለሽ ፍጽም ሰው ነው ማለት ነው።

*ቴታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ስለ ራሱ ተናፅሯል፡-*

በተለያየ ስፍራ ስለ ራሱ ማንነት ጌታ ሲናገር «የሰው ልጅ» በማለት ይናገር ነበር።ይህም ሰው መሆኑን ለማመልከት የተጠቀመበት ሐሳቡ ነው። ዮሐ8:28,40,5:27,10:33, ሉቃ22:22 ማቴ4:2

*በሕጅዉቱ በሚጸርጋቸው የዕለት ተዕለት ኑሮው፡-*

ክርስቶስ በምድር በኖረበት ጊዜ በማንኛዉም ሰዉ ላጁ ጁታይ የነበረው አጠቃላይ የሰው ባሕሪና አኗኗር ጁታይበት ነበር።

ለምሳሌ ፡- 1ኛ/ ስሜታዊ ባሕሪዎች ነበሩት

እንደ ሰው ተርቧል ተመግቧል ማተ4:1-4 21:18 ሉቃ22:14

እንደ ሰው ተጠምቷል ዮሐ19:28

እንደ ሰው አልቅሷል ዮሐ11:35

እንደ ሰው ተኝቷል ማቴ8:24

ከኃጢያት በስተቀር እንደ ሰው በነገር ሁሉ ተፈትኗል ዕብ2:18

እንደ ሰዉ በእፅሩ ከቦታ ወ ቦታ ተ ዉሯል

2ኛ/ በሌሎች ዘንት ሰዉ እንደ ሚጠራው ተጠርቷል ሰው ተብሏል

በመጥምቁ ዮሐንስ ዮሐ1:30

በሐ ርጸዉ ጁዓሮስ ሐ 2:22

በሐ ርጸዉ ጁዉሎስ ሐ 13:38

በሌሎች በብዙዎች ዮሐ7:27

አይሁዳዊ ሰው እንደ ነበርም ይታወቅ ነበር ዮሐ4:9

እንደ ሰዉ ክትሜዉ ጁታወቅ ነበር ዮሐ8:57

3ኛ/ እንደ ሰው ስሜቱን የሚገልጥበት መንገድ ነበረው

- ውስጡን ሐዘን በቃለት ተናገረ«...ሊያዝን ሊተክዝም ጀመር፡፡ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች...» ማቴ26:36-44
- በዙሪያው ባሉት ሰዎች አመለከከት ትክክለኛ አለመሆን የውስጡን ሀዘን በቁ ቆለቷ «... በቁጣ አያቸው...» ማር3:5
- በጌተሰማኔ በተያዘበት ምሽት እጅግ ፈርቶ ለአርታ እንዴት እንደ ለ ሉቃስ ሲናር «... በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፡፡» ሉቃ22:44

*ሰው የመሆኑ ጥቅም ለክርስትና ሃይማኖት:-*

እስከ አሁን ያነሳናቸው ሐሳቦች በሙሉ ክርስቶስ በእርግጥ ሰው ነው አልያም ፍጹም ሰው ነው ልንል የቻልንበትን መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ለማብራራትና ትክክለኛ መረጃ ከመስጠት አንጻር ሲሆን ነገር ግን ክርስቶስ ሰው መሆኑ ለክርስትና ሃይማኖት ትርጉሙ ወይም ጠቀሜታው ምንድር ነው? ሰው እንዲሆን አስገዳጅ ሁኔታ አለ ከለስ ምንድር ነው ? የሚለው ነጥብ ደግሞ መነሳት ያለበት ሁለተኛው ጉዳይ ነው፡፡ክርስቶስ ሰው እንዲሆን ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶ አሉ፡፡

*1. በአንዱ በአዳም ምክንያት ያ ነውን የዘለዓለምን ህይወት ለመመለስ፤*

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ላይ በምዕራፍ 5:12-21 ትረስ ባለው አል ውስዓ በአንዱ አዳም አለመታዘዝ ምክንያት ኃጢያት ወደ ዓለም ቶ በሀጢያት ምክንያት ደግሞ ሞት ለሰው ሁሉ እንደ ደረሰ ከገለጸ በኋላ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ የሆነው የዘለዓለም ሕይወት ደግሞ ወደ ሰው ሁሉ መጣ ይለናል፡፡ በሰው አለመታዘዝ ምክንያት የመጣው ሞት በሰው መታዘዝ ደግሞ መሰበር ስላለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆን ፍጹም መታዘዝን ለእግዚአብሔር በማሳየት የዘለዓለምን ሕይወት ወደ ዓለም ማስገባት ስለ ነበረበት ሰው ሆነ፡፡ « ... በአንድ ሰው በደል ብዙዎች ሞተዋልና ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ፡፡» ሮሜ5:15

*2. የሰው ልጆች የተያዙበትን የኃጢያትን ዕዳ ለመክፈል፤*

ክርስቶስ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ፊት በሀጢያት ምክንያት ተጠያቂ ባለ ዕዳ ለሆነው ሰው ል በሙሉ ምትክ በመሆን ያለባቸውን የሀጢያት ዕዳ ለመክፈል ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ሰው መሆን አስፈለገው፡፡በዚህም ምክንያት በነቢያትም ሆነ በአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ውስጥ የተጠራበት ልዩ መጠሪያም ነበረው፡፡ «እነሆ የዓለምን ሀጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡፡»ዮሐ1:29,36 ኢሳ53:7

*□እፅአብሔር በግ በሚል መጠሪያ ወደ ምድር የመጣበትን ዓለማ የሚገልጥ ስያሜ የተሰጠው ከዚህ በመነሳት ነው። በእርግጥ ይህ አገላለጥ ከብሉይ ኪዳን የሀጢያት የማስደምሰስ ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት ያለው አከሔድ በመሆኑ ምክንያት ነው እንደዚህ ዓይነትን ቃላት የተጠቀሙት።ለሕዝቡ ሁሉ ስለ □ሀጢጸታቸው ማስተሰረይ የሚሆን ደም መፍሰስ ስላለበት የበግ ደም በሊቀ ከህኑ በየአመቱ አንድ ጊዜ ይቀርብ ነበር። ክርስቶስ ግን በበግ ደም ሳይሆን በገዛ ደሙ ከለብን የሀጢያት ዕዳ እኛን ነጻ ከወጣ በኋላ ወደ እውነተኛይቱ መቅደስ ገብቷል። የገዛ ደሙን በማፍሰስ ሊያስተሰርይለን የግድ ሰው መሆን አስፈልጎታል።* **ክብ9:11-12**

*በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በደሙ የተዋጀች የእግዚአብሔር ሆናለች።የሐዋ20:28 ከዚህ መሰረታዊ ሐሳብ በመነሳት መዋጀት የሚለው የቃሉን ትርጉም ለመረዳት ብንሞክር የራስ ማደረግ መልሶ ባለቤት መሆን የሚሉትን ጽንሰ ሐሳቦችን ሁሉ ያከትታል።ምክንያቱም የኮርማዎች፣ የፍየሎች እና የበጎች ደም ስለ ሕ□ቡ ሀጢያት ይቀርቡ የነበሩትም በዚህ በመዋጀት ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ ነው፣የሰውን ቦታ ተ□ተዉ በመቅረባቸው።*

*ሌላው በዚህ ውስጥ መጠቀስ ያለበት □እውነት □ሀጢጸተኛ የሆነ ሁሉ የሀጢያቱን ብድራት መቀበል ወይም ደግሞ መቀጣት አለበት። ጸለበለ□ጸ እግዚአብሔር በራሱ □ትቅ እንዳይደለ ያሳያል።ስለዚህ ክርስቶስ በሰው ቦታ ሆኖ ስለ ብዙዎች የብዙዎችን ቅጣት በመከራው፣ በግርፋቱ እና በመስቀል ላይ በከፈለው መስዋዕትነቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ ጭምር ነጻ አደረገን።□እርሱ ስለእኛ ሀዓ ሀ□ሆነ እኛ በርሱ ቦታ ጻድቃን ተባልን።ይህንን ለመፈጸም ሰው መሆን አስፈልጎታል። ሮሜ3:25-26 «... ራሱም □ትቅ እንዲሆን...»*

## *2. ሞትን በሞቱ ድል ለመንሳት፤*

*በአንዱ በአዳም ምክንያት □ሀጢያት ወደ ሰዎች ሁሉ እንደ □ረሰ □ሀጢያትም ደሞወዝ ሞት በመሆኑ ምክንያት ሞት ለሰው ልጅ በሙሉ ደረሰ። የሞት ሀጁል እና ስልጣን ከሰው ልጆች ላይ ለዘላለም የማይነሳ ቀንበር ሆነ።ስለዚህ በሞቱ ሞትን ድል ለመንሳት ክርስቶስ ሰው ሆነ።* **ክብ2:19** *«እንግዲህ ልጆቹ በስጋና በደም ስለሚካፈሉ □እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ስልጣን ያለውን በሞት □እንዲሽር ... ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ □እንዲያወጣ በስጋና በደም □እንዱሁ ተከፈለ።» ጁህ አባባል ግልጽ እና ቀጥተኛ ነው ስለምን ዓላማ ክረስቶስ ሰው መሆን□እንዳስፈለገው ይናገራልና።*

*በዚህ ምክንያት ክርስቶስ ከሙታን በኩር ሆኖ ተነሳ።□እኛም የዘላለምን ቤዛነት በደሙ ያገኘን ሁላችን እርሱ ከሞት እንደ ተነሳ እኛም □ዕሞ□እንነሳለን።* **1ቆሮ15:21-23** *«አሁን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና።ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን የሆናሉና።*

### *4. በሰው ልጅ በደል ምክንያት በክፉ መንፈሳዊ ሰራዊት የተነጠቀውን ስልጣን ለመመልስ*

አስቀድሞ በአዳም ፍጹም እጅ የነበሩ ምድርን የማስተዳደር የመግዛትና ለሞት እና ለሀጢያት ያለመሸነፍ የነበረ የሕይወት የበለይነት ሁሉ በሀጢያት መተላለፍ ምክንያት ከአዳም አምልጠዋል በክፉ እ□ም ውትቀ□ል □እነዚህ መብቶችና የበላይነቶች ሁሉ ወደ ሰው እጅ ለመመለስ ክርስቶስ ሰው መሆን አስፈልጎታል። ክብ2:15 «... □እርሱም ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው... በሥጋና በደም እንዲሁ ተከፈለ።»

ክርስቶስ ሰው በመሆኑ ምክንያት ሞትን በመሞት በሞት ላይ ስልጣን ያለውን ሽሮአል ሁሉም ተገዝቶለታል። «አለቆችንና ባለሥልጣኖችን በመስቀሉ ድል ነሥቶ ትጥቃቸውን ካስፈታ በኋላ ምርኮኞች ሆነው በይፋ እንዳታዩ አደረጋቸው።» ቆላ2:15 የ1980 ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ

### *5. እግዚአብሔር አብን ሊገልጥልንና ሊያሳየን፤*

እግዚአብሔርን ማንም አላየውም አይቶትም አያውቅም ነገር ግን በነቢያቱና እርሱ በሚልካቸው ባሪያዎቹ ስለ እርሱ ባህሪ፣ዓላማውን እና ፈቃዱን እንድናውቅ ይረዱናል □እንጂ ሙሉ ማንነቱን አልገለጡልንም። «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጅ እርሱ ተረከው።» ዮሐ1:18

ክርስቶስ በሚያደርጋቸው ሥራዎቹ በባሕሪዉ እና በትምህርቱ ሁሉ እግዚአአብሔር አብን አሳይቶአል። □ማ□ርቆዉ ሁሉ □እኔን ሳይሆን የላከኝ ፈቃድ ነው! □እኔን ያየ አብን አይቷል! ብሏል□ ኢየሱስ።ዮሐ14:8-11

በዮሐ17:6 «ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው።» ስሙ የማንነቱ መገለጫ □እንጂ መጠሪያው አይደለም ስለሆነም የገለጠላቸው እግዚአብሔር አብን □እንጂ ስም አይደለም ያስተማራቸው።በአጠቃላይ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሙሉ መገለጫ ስለ ነበር ሩቅ የነበረው እግዚአብሔር ሰው የሆነው ክርስቶስ በመከከላችን በማደሩ ምክንያት የዘላለም ክብሩን አየን።ዮሐ1:14 በዚህ ምክንያት ክርስቶስ ሰው መሆን አስፈልጎታል።

### *1. አምላክ የሚፈልግብንን □ሕይወት ኑሮ ምሳሌ ሆኖ ሊያሳየን፤*

እግዚአብሔር በዘላለማዊው ዕቅዱ ሰውን ሲፈጥር በእርሱ አምሳልና መልክ ነው።ይህ ማለት እግዚአብሔር □እንደ ሰው ያለ ቅርጽና ይዘት አለው ለማለት □እንዳልሆነ ሁላችን □እንረዳለን ነገር ግን የውስጡ ማንነታችን□እርሱን እንዲመስል ወድዶአል። ጹህ መል□ በሀጢያት ምክንያት ከሰው ልጆች ሕይወት ታጥቷል።ወይም ሀጢያት ባመጣው መርገም ምክንያት የቀድሞ በእግዚአብሔር የተፈጠረው ፍጹማዊው ማንነታችን ተበላሽቷል።አሁን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ባገኘነው ጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ ሀይልና ክብር የተነሳ □እግዚአብሔር አምላክ የሚጠብቅብንን የህይወት ደረጃ በኑሮአችን □እንድናሳይ ሰው

በሆነው በክርስቶስ ሕይወት አሳይቶናል ርሱን እንደ መስኪያ ደግሞም እንደ ሞዴል በማሳየት እርሱን እንድንመስለው አዘናል፡፡የሕይወታችን መስኪያ የመጨረሻው ደረጃ ሰው ሆኖ በምድር ላይ የተመላለሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ኤፌ4:24 1ቆሮ11:1 1ተሰ1:6-8

**ፍጹም አምላክ ነው**

ስለ ክርስቶስ ማንነት በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ ምክንያት ክርስቶስ ራሱ በምድር በነበረበት ወቅት እንኳን ብዙዎች ያልተቀበሉት ብዙዎችም የተሰናከሉበት እርሱም ሰዎች ስለ እኔ ምን ይላሉ ብሎ የጠየቀበት አነጋጋሪ ሃሰብና ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሰው ነው ካልን በኋላ አምላክ መሆኑን መልሰን መቀበል ለገዛ ሒሊናችን ስለ ሚከብድ በተጨማሪም በምድር ስለ ተመላለሰ ሰው መሆኑን ለመቀበል ብዙ ባንቸገርም አምላክ ስለ መሆኑ ግን ብዙ ችግሮች እና ጥያቄዎች በውስጣችን ይፈጠራሉ ስለሆነም ሰው ስለ መሆኑ እና ሰው የመሆኑ ጥቅም ለክርስትና ሃይማኖት ምን እንደሆነ እንደተመለከትን ሁሉ ፍጹም አምላክ ስለ መሆኑ ደግሞ በሚቀጥሉት ዝርዝሮች ውስጥ ግንዛቤ ለማገኘት እንሞክራለን፡፡

ክርስቶስ ዓምላክ ስለ መሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን ማቅረብ ብንችልም እንኳን አጥጋቢ አስረጅ የምናቀርበው ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ብቻ ነው፡፡

*1.ቀዓተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች፤*

ዮሐንስ ሐዋርያው በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ አስቀድሞ በዚሁ ትምህርታችን ዉስዓ □እንደተመለከት ነው ክርስቶስ በቅድመ ሁናቴው ማለትም በሥጋ ከመምጣቱ በፊት ማን እና እንዴት እንደ ነበር ሲቶል□፡፡ቃልም□እግዚአብሔር ነበር ይለናል፡፡ዮሐ1:1 ይህ አባባል እርሱ ራሱም ዓምላክ ነበር ማለት ነው፡፡

ሐ□ርጸዉ ቼዉሎስ በዕብራዊያን መልዕክቱ በቀጥታ□ስለ ክርስቶስ ማንነትተናግሯል፡፡ ዕብ1:3«...□ረሱም □□ብሩ መንጸባረቅና የባሕሪው ምሳሌ ሆኖ ...» ``The Son is <u>**the radiance**</u> of God's glory and the <u>**exact representation**</u> of his being ...``ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረት ቺ□ በእርፅዓም □እግዚአብሔር ማንነት መገለጫ □እና የማንነቱ መስታወት □እርሱን በትክክል የምናይበት ነበር፡፡ በ□ህም ሲቀዓል በቀዓታ ሲናገረ ስለ ልጁ «አምላክ ሆይ» «ጌታ ሆጂ» ብሎ ጁቷራ□ል፡፡ ክብ1:8,10

ሐዋርያው በሮሜ መልዕክቱ ላይ ደግሞ «አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መ□፡፡□እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ <u>ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው</u>፤አሜን፡፡» ሮሜ9:5 ለዘለዓለም የሚለው ቃል በትኩረት መታሰብ ያለበት ነው፡፡ዘላለም ጅማሬም ፍጻሜም የሌለው ለማለት ነው፡፡አምላክነቱ □ማሬም □ለዉም □ፅሞም አ□ሜ □ለዉም፡፡ ብሎ ከገለጸለው በኋላ ለቲቶ በጻፈው መልዕክቱ ደግሞ «... የተባረከውን ተስፋችንን □ርሱም <u>□ታላቁ የአምላካችንንና</u> □መትሀነታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር

መቆለዓ እየጠበቅን... »ቲቶ1:12 በማለት በተለየ አገላለጥ ታላቁ አምላክ ጁለ□ል! □እንዲሁም ጴጥሮስ «በአምላካችንና በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ።» 1ጴዓ 1:1 በማለት አምላክነቱን ለማሳየት ሞክረዋል።

*2. ቴታ እርሱ ራሱ ስለ ራሱ ያለውና/የተናገረውና ጸስተማረው፤*

በቀዓታ ስለ ራሱ ዓምላክነት በብዙ ሥፍራ ባይናገርም እንኳን የሚያደርጋቸው እና አልፎ አልፎ የሚናገራቸው ንግግሮች ማንነቱን ይገልጡ ነበር።

- □ሐ10:30 «□እኔና አብ አንድ ነን።» ይህን በማለቱ በአይሁዶች ዘንድ እራሱን አምላክ በማድረጉ ምክንያት ሊወግሩት ድንጋይን አነሱ።
- ራዕ1:8 «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ ፦ አልፋና ያሜጋ □እነ ነኝ ጁላል።» ከዚህ ንፅፅሩ የምንረዳው መጀመሪያም መጨረሻም እኔ ነኝ ሲል ከእርሱ ቀ□ሚ □ፅሞም የሁሉ ነገር ማጠቃላያ □እርሱ ነው። የአምላክነቱ ግብር ነው።
- ማቴ26:59-66 «...□ሰዉ ል□ በሀይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ□ ታያለችሁ አለው።...» ይህንን በመናገሩ □እግዚአብሔርን □እንደ ተሳደበ ቆጥረው መከራ አደረሱበት።
- ማቴ13:41 «የሰው ልጅ መላክቱን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ጁለቅማሉ ወ□ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል... » በዚህ የጌታ ንግግር ውስጥ የምንመለከተው ግልጽ ሃሳብ የመላክቱ ባለቤት እርሱ አንደሆነ ይገልጻል።

*3. ቴታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያደርጋቸው ድርጊቶች ዓምላክነቱን ይገልጣል፤*

- ማር2:5«... አንተ ልጅ □ጢያትህ ተሰረየችልህ አለው።» እምነተቸውን አይቶ ይህን በማለቱ ለሽባዉ ልጅ በዙሪያ ባሉት አይሁዳውያን ዘንድ□እራሱን□እግዚአብሔር አድጎ በመናገሩ ስድብ ነው አሉ።ነገር ግን □እርሱ ይህንን ለማድረግ የሚችል አምላክ □እንዲሁም ስልጣን እንዳለው ለማሳየት ነበር።

- በተራራው ስብከቱ ሙሴ በሕጉ እንዲ በሎአችኋል እኔ ግን□እላችኋለሁ የራሱን በማስተማሩ □እንደ ጻሕፍት ፈሪሳዊያን ሳይሆን □እንደ ባለ ስልጣን ስላስተማራቸው በትምህርቱ ተገረሙ።□እንደ ሕግ ተቀባይና አስፈጻሚ ሳይሆን □እንደ ሕግ በለቤት ወጅም እንደ ሕግ ሰጪ እኔ ብሎ በማስተማሩ□እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራ የሚችለውን ስራ በመስራት □ራሱም □እግዚአብሔር □እንደ ሆነ ማየት ይቻላል።

*4. የመለኮት ባሕሪያት በእርሱ ጁታጁ ነበር፤*

« በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራል::» ቆላ2:9 መለኮት ስንል ዓምላክን አምላክ የሚጸሰኙት መገለጫዎቹ ሲሆኑ እነዚህም የትኛውም ፍጥረት ሊሰራ የማይችለውን ስራ እና የባሕሪ ማንነት ነው የሚያሳው::

- ሁሉን ያውቃል ቆላ2:2-3 ራክ2:23
- በሁሉ ስአራ ጁቁኛል ማተ18:20 28:20
- ሁሉን ይችላል ዮሐ5:19
- ዘላለማዊ ነው ዮሐ1:1-2

📖 በአጠቃላይ እስካሁን መመልከት የቻልነው እውነት ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው እንዲሁም ፍጹም አምላክ ነው ! የሚል መሰረታዊ የክርስቶስ ማንነት ላይ ያለንን እምነት ነው::

*በወንጌላዊያን አማኞች መለኮት እና ሰብዓዊነቱ ያለው ግንኙነት ሲገለጥ፡-*

በቀደሞት የእምነት አባቶች መካከል በተደረጉት ታላላቅ ስብሰባዎች እና ውይይቶች ስለ ክርስቶስ አምላክነት እና ሰውነት የአምነት አቋም መግለጫ ተደርጎ የተወሰደው ሐሳብ "<u>ክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባህርያት የማይደባለቁ ፣ የማይለወጡ የማይከፋፈሉ፣ የማይነጣጠሉ</u>" የሚል ነበር። በመሆኑም አምላክነቱ አልያም ሰውነቱ በሚል ሐሳብ ነጣጥሎ ማስተማርም ሆነ አስረጅ ለመስጠት መነሳት በክረስቶስ ማንነት ላይ መሰረታዊ ችግር ማምጣት ይሆናል። በእርግጥ ይህ የአንድ ባሕርይ እና ሁለት ባሕርይ አስተምህሮ የምስራቁን እና የምዕራቡን አማኞች ለሁለት የከፈለ ሐሳብ ሆኖ ተገኝቶአል። በዚህም ሳቢያ የምስራቁን መንገድ "የአንድ ባሕርይን ባህል" ተከትላ የኖረቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን። የካቶሊክ ቤት ክርስቲያን ደግሞ "የሁለት ባህርይን ባህል" ይዛ ተጓዘች።

**ሁለት ባሕርይ በአንድ አካል**

ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ይዞአል ማለት መለከት-ሰው ነው ማለት ነው።።መለኮታዊው ባሕርይና ሰብኣዊው ባህርይ በአንድ ማንነት አሉ ማለትን ለማስረዳት ነው። ክርስቶስ በማንነቱ ሁለት ሳይሆን አንድ "እኔ" ነው። በመሆኑም በሁለት ባሕርይ እየኖረ አንድ እኔነት ነው ያለው። ክርስቶስ እኔ ሲል "እኔ ሰው የሆንኩት" በማለት እራሱ አይገልጥም፤ ክርስቶስ እኔ ሲል "እኔ መለኮት" በማለት እራሱን አይግልጥም ይልቁን በሁለቱም ባሕርይ እኖረ እራሱን ግን ሲገልጥ በአንድ እኔነት ነው።።ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ነጥቦች ከዚህ በታች መመልከት ይቻላል፤እነዚህን ለአብነት ያህል ነው

- በመለኮት መጠሪያነት በሰው ሥራ የተገለጠባቸው ክፍሎች

- ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፤1ቆሮ2፡8
- አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን። ሮሜ9፡5
- የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? ሉቃ1፡43
- ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና። ሉቃ2፡11

- ***በሰው መጠሪያነት በመለኮት ሥራ የተገለጣበቸው ክፍሎች***
    - ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። ዮሐ3፡13
    - እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል? ዮሐ6፡62
    - ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥ በዚያን ጊዜ ሽባውን። ተነሣ፤ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው።ማቴ9፡6
    - የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ማቴ24፡29-31

**ጠቅለል ባለ ሟኩ**

- ***የመለኮት ባህርይ ጎልቶ የታየባቸው ነበሩ -ዮሐ8፡58***
    - ***ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።***
- ***ሰብአዊ ባህርይ ጎልቶ የታየባቸው ነበሩ -ዮሐ19፡28***
    - ***ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ። ተጠማሁ አለ።***

➔ **በዚህ ሁሉ ግን ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ በአንድማንነት የማይደባለቁ ፣ የማይለወጡ፣ የማይከፋፈሉ፣ የማይነጣጠሉ ሆነው ያለ ማንነት ያለው ነው።**

***የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የእምነት አቋም***

- ***ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባህርይ በተዋህዶ ነው!***
- ***የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ እንደ እሳትና እንደ ብረት ተዋሕዶ ነው፡፤***
- ***ተዋህዶ ቱሳሔ፣ ምንታዌ፣ ቡዓዴ ፣ውላጤ፣ፍልጠት የሌለበት በተዐቅቦ ጸንቶ የሚኖር መኖት በሁላችንም ዘንድ የሚካድ አይደለም።***
    - ***(ቱሳሔ - መቀላቀል ፣ መደባለቅ ማለት ነውገጽ ፺፷)***

- (ቡዐዴ - ተዋሕዶ ተሳጽቆ ተቃርቦ ነው ማለት ነው፤)
- (ፍልጠት - ከተዋሕዶ በኋላ የሚመጣ መለየት ማለት ነው፤)
- በዚህም አካኂን ቱሳሔ ውሳጤ ፍልጠት ቡዐዴ ምንታዌ ሳይኖረበት ቃል ርቀቱንም ምልአቱን ስፋቱን ሳይለቅ ትስብእትም ግዘፉን ውሱንነቱን ሳይለቅ በተዐቅቦ እንደ ተዋሐደ እናምናልን።
- (የሃይማኖት ሚዛን ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ገጽ 105 ነሐሴ 1/1954 ዓ.ም በትንሳዔ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት የታተመ አዲስ አበባ)

## ለ. ክርስቶስ ራሱን ባዶ ማድረጉ [Kenosis] ኪኖሲስ

ክርስቶስ እራሱን ባዶ አደረገ የሚለው ክፍል በፊል2፡6 ላይ ያለ ቃል ሲሆን አውዱ በመሰረቱ በክርስቶስ የነበወረውን የትህትና ኑሮ እና መንገድ የፊልጵስዩስ ሰዎች ደግሞ እንዲከተሉ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የምንባቡ ክፍል ስለ ትሕትና ለማስተማር ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ክርስቶስ ራሱን ባዶ አደረገ ስንል ለማለት የተፈለገው ራሱን እንደሚገባ አለመቁጠር /ራስን ዝቅ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ጌታ አምላክ ሆኖ ሳላ ለክብሩ እና ለማንነቱ የማይመጥንን ደረጃ በፈቃዱ ለሰዎች ልጆች ጥቅም ሲል ሰው መሆኑ፣ የባሪያን መልክ መያዝ ፣ እስከ መስቀል ሞት ደረስ እራሱን ዝቅ አድርጎ መታዘዙ የሚገባው አይደለም ግን አደረገው፡፡ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርም ክርስቶስን ያለ ከፍ ከፍ አደረገው፡፡

## ሐ. ክርስቶስ ኃጢያት ሊያደርግ አለመቻሉ

➔ ክርስቶስ ከኃጢያት ነፃ የሆነበት ምክንያቶች

እንግዲህ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑን እና ፍጹም ሰው የመሆኑስ ጥቅም ምን እንደ ሆነ በጥቅሉ ተመልክተናል፡፡ነገር ግን ከዚህ ርዕስ ሳንወጣ መታየት ያለበት ጉዳይ ክርስቶስ ፍጹም ስው ነው ሲባል ከሀጢያት ንክኪ የነፃ መሆኑን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የክርስቶስ ደም የሰዎችን ሀጢያት ለማስተሰረይና ለማንጻት ያለው ጉልበት እንዱሁም አቅም ላለማሳነስ ይልቁን ለማጉላት የረዳልና፡፡በሌላ ወገን ደግሞ መከላከል ያለብን ልዩ ሀሳብ እንዳይፈጠር ነው፡፡ደሙ የሰው ደም ሳይሆን የመለኮት ደም ነው ከሚለው እንግዳ ትምህርት ለመዳን፡፡ ስለሆነም፡-

1ኛ/ ክርስቶስ ከወንድ ፈቃድ አልተወለደም፡፡የተጸነሰው ከመንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ምክንያት ቅዐስ እግዚአብሔር ልጅ ተብላል፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ከሀጢያት ተጠያቂነት በራሱ ንጹሕ ነው፡፡ ማቴ1፡18

2ኛ/ ክርስቶስ የተወለደው ከድንግል ሴት ነው፡፡መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ከድንግል ስለ መወለዱ ይናገራል የመጽሐፉ መሰረታዊ ሃሳብ ከዚያ በፊት ማሪያም ምንም አይነት ህብረት ከወንድ ፉር እንዳልነበራት እና የዘለዓለሙ የልዑሉ ጣልቃ ገብነት ይህን እንዳደረገ ለማሳየት ነው፡፡እንዴት

ይቻላል ለሚሉ ሁሉ መልሱ መላአኩ እንዳለው «ለእግዚአብሔር ሚሳነው ነገር የለም!» ነው መልሱ::ሉቃ1:26-38

3ኛ/ የመጀመሪያው ሰው አዳም ከመሬት ሲሆን ጅማሬው ሁለተኛው አዳም የተባለው ክርስቶስ ግን ከሰማይ የመጣ ነው::ከእግዚአብሔር ብቻ የሆነ የሰው ጅማሬ ያላቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሁለት ብቻ ናቸው::የመጀመሪያው አዳም ሲሆን ሁለተኛው ሰው ደግሞ ክርስቶስ ነው::ሌላው የቀረው ሰው በምድር ላይ የነበረው ዛሬም ያለው ወደፊትም የሚኖረው የመጣው አምላክ ባዘዘው የመባዛት ሥርዓትን ተንተርሶ እና ተከትሎ ነው:: በዚህ ምክንያት ክርስቶስ ከሀጢያት ፍጹም የነጻና □ኛን ሊያድነን የሚችል ብቸኛ ሰው ነው::2ቆሮ15:42-47

## መ. በክርስቶስ ማንነት ላይ የተነሱ የስህተት ትምህርቶች

□ክርስትና ሃይማኖት ከመጀመሪያዎቹ ሐዋሪያት ጀምሮ የተለያዩ የስህተት አስተምህሮዎች መነሳታቸውና □እድገቱን ለመግታት የሞከሩበት ሁኔታ ቢኖርም እንኳ ሁሉን አልፎ እዚህ አሁን ባለንበት ዘመን ላይ ደርሰናል::ነገር ግን በየዘመናቱ ተነስተው ከነበሩት የሐሰት ትምህሮቶች መካከል ዋነኛው በክርስቶስ ማንነት ላይ የሚነሳው ትምህርት ነው እሲቲ የመጀመሪያዎቹ ምን ዓይነት መልክ እንደ ነበራቸው እንመልከት::

### *1. ሞናርክያኒዝም*

- የአስተምህሮው መሪ ቴ- □ፌስ

- አስተምህሮው:- ኢየሱስ ሲጠመቅ ክርስቶስ ሆነ □እንጂ አስቀድሞ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው ይኖር የነበር ነው:: ከሞት በመነሳቱ ምክንያት አብ የተለየ የልጅነትን ክብር አጎናጸፋው::ዓለምን ይመራ እና ያስተዳደር የነበረው እግዚአብሔር ሲሆን እርሱም አንድ የሆነ ማንነት ያለው ነው እንጂ በሦሥትነት የሚኖር አይደለም::

### *2. ሳቤልያኒዝም*

- የአስተምህሮው መሪ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሶስተኛው ክፍለ ዘመን በሮም ይኖር የነበር **ሳቤሊ□ስ** የሚባል ግለሰብ ነው::

- አስተምህሮው:- በእርፅዓ እግዚአብሔር ሶስት ማንነት የለውም ነገር ግን በተለያየ ጊዜ እራሱን ለሰዎች ልጆች በሶስት ዓይነት ገጽ□ወጁም ሞት ጁፅለ□ል እንጂ እርሱ አንድ ነው ብሎ አስተምሯል::ይህንንም ሲያብራራ ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን እራሱን እእንደ አባት አድርጎ ሲገልጽ በአዲስ ኪዳን ደግሞ በወንጌል በክርስቶስ ወልድ ሆኖ፣ከበዓለ ሃምሳ በኋላ □ፅሞ እራሱን መንፈስ ቅዱስ አድርጎ ገልጿል ይላል::

### *3. አሪያኒዝም*

- የአስተምህሮው መሪ **አሪዮስ** ሲሆን
- አስተምህሮው:- ክርስቶስ በእግዚአብሔር  አብ ከሌሎች ከየትኛውም ፍጥረት በፊት የተፈጠረ ሲሆን ነገር ግን መለኮታዊ ከሆነው ከአብ ጋር ተመሳሳይ ተፈጥሮ ያለው ሰማያዊ ማንነትን የተላበሰ ነው።

### *4. ማሲዶንዝም:-*

- የአስተምህሮወ መሪ **መቅዶንዮስ**
- አስተምህሮው :- መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው።

### 5. ንስትሮንያኒዝም

- የአስተምህሮው መሪ **ንስጥሮስ**
- አስተምህሮው:- ክርስቶስ በማንነቱ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ አይደለም።የመለኮት ባሕርይው የሰውነት ባሕርይውን ተቆጣጥሮታል።

## አሁን ባለንበት ዘመን

- አስቀድመን በጥንት ቤተ ክርስቲያን የተነሳውን የስህተት ትምህርቶችን ተመልክተናል በሚቀጥሉት ሃሳቦች ደግሞ በገዛ ዘመናችን ያሉትን በተለይ በክርስቶስ አስተምህሮ ላይ የስህተት አቅጣጫዎች ላይ ብቻ በማቶከር እንመለከታለን።

### 1. □□ሆቫ /□ሖ□/ ምስ□ር

በክርስቶስ ማንነት ላይ ያላቸው አስተምህሮ □እርሱ የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ ፍጡር እንጂ መለኮትነት □ለዉም።ይህም አስተምህሮ በጥንት ቤተ ክርስቲያን ከተነሳው አሪያኒዝም ጋር ተመሳሳይ ገጽ አለው።

### 2. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን

በእግዚአብሔር ሦሥትነት ላይ ግልጽ የሆነ አስተምህሮ አላቸው።የአንዱ አምላክ በሶስት ዓይነት መልክና መንገድ መገለጽ ነው □እንጂ አምላክ እግዚአብሔር አንድ ነው በርግጥም ሶስት አይደለም።ስለዚህ ክርስቶስ እግዚአብሔር የተገለጠበት ስጋ ነው።በሚል መሰረታዊ ሃሳብ ዙሪያ ያጠነጥናል።ይህም ከሳቤሊያኒዝም አስተምህሮ ጋር ተቀራራቢነት አለው።

# 6.የክርስቶስ ባህርይ እና ስሞቹ

## ባህርይው

የክርስቶስን ባሕርይ ለማወቅ ስንነሳ መዘንጋት የሌለብን መሰረታዊ □እውነት በእግዚአብሔር ሦሥትነት መሐል ያለው የባሕሪ አንድነትን ነው:: ስለ ሆነም ክርስቶስ ከእፀ□አብሔር አብ የተለየ ባሕርይ □ለዉም::የአብ ባሕርይ□ርሱም ባሕርጁ ነው፣ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ :: ለምሳሌ:- ታማኝነቱ፣ ታጋሽነቱ፣ ጻድቅነቱ፣ ቅዱስነቱ፣የዋህነቱ፣ፍቅር መሆኑ እና ቸርነቱ ሁሉ በዋናነት የሚጠቀሱ ሆነው ለምሳሌ ያህል ግን የሚከተሉትን በማብራራ ማየት ይቻላል::

ፍቅር ነው:- አቅሩን ጌታ በሚያደርገው ሥራ አሳይቶአል::ጳውሎስም ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሲናገር ርዝመቱ ከፍታው ጥልቀቱ ከመታወቅ የሚያልፍ ነው ብሎአል::ኤፌ3:18-19 በ□ህ □ለም ያሉትን ወገኖቹን እስከ መጨረሻ ወድዶአቸዋል:: ዮሐ13:1 □እንዲህ ከሆነው ፍቅሩ ማንም ሊለየን □እንደ ማይችል የእግዚብሔር ቃል ይናገረል:: ሮሜ8:35 «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል::»

አ□ም ቅ0 ስ:- አስቀድመን ክርስቶስ ከሀጢያት ነፃ ስለ መሆኑ በሰፊው አንስተናል::በምድርም ሳለ አንዳችስ እንኳ በደል አልተገኘበትም::በሀጢያትም ጌታ አይከሰስም::1ጴጥ22-23 ስለ እኛ ኃዓ ክ ተባለ እንጂ እርሱ ፍጹም ጻድቅ ነው:: 1ቆሮ5:21 «...ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን...»

ትሑት:- ቴታ በአገልግሎቱ ሸክማቸው የከበደባቸውን ሁሉ ወደ እርሱ □እንዲመጡ ሲጋብዝ □እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ አለ::ማቴ11:28-29 ስለዚህ ብዙዎችን ሲቀበል ለሁሉም ምቹ ሆኖላቸው ነበር::ምክንያቱም □እርሱ በማንነቱ ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለድሆች ጥቅም በመኖሩ ነው::ይህ ስራዉ ነው ትሑት ያሰኘው ደግሞም በመለኮት ማንነት በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ የመለኮት ክብሩን ትቶ ሲመጣ □እስከ መስቀልም ሞት ድረስ እ□ታዘዘ ሲሆን ዘለዓለማዊ ክብሩ እንደ ሚቀማ ነገር አልቆጠረውም::ፊል2:5-8 ስለዚህ የመልዕክቱ ጸሐፊ ይህ የክርስቶስ የትሕትና ሐሰብ በእናንተም ዘንድ ይሁን ይላቸዋል:: □ፅሞ □ሬ ለእኛም ይለናል::

## ስሞቹ

የኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደ ሰው ያለ መጠሪያ ብቻ ሳይሆን የማንነቱ መገለጫዎች ናቸው::ስለዚህም በሚሰራቸው ስራዎቹና ለእኛ በሆነልን ሁናቴ በዚያ ይጠራል::ከእነዚህም መካከል በአብዛኛው የተጠቀሱት በአዲስ ኪዳን መጽሕፍት ውስጥ ነው::

***ኢየሱስ*** **:-ማቴ1:20-21** *መልአኩ ለማርያም □□ ኛ ለዮሴፍ በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተጸነሰው ሕፃን ካስረዳው በኋላ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ባለው መሰረት የተሰጠው ስም ነው።ትርጓሜውም አዳኝ ማለት ነው።ሕዝብን ሁሉ ከሀጢያት ስለሚታ□ፅ እና ስለሚያድን ስሙም ከሀጢያት □ሚታደግ አዳኝ ተባለ።*

***ክርስቶስ*** **:-ዮሐ1:42** *«… መሢሕን አግኝተናል አለው ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው።በመሰረቱ የግሪክ ቃል ቢሆንም በዕብራዊያን ዘንድ ግን የሚጠራው መሢሕ በሚል ነው።ስለዚህም አይሁዶች በማንነቱ ግራ ሲጋቡ አንተ መሢሑ ነህ ? ይሉት ይጠይቁት ነበር።ይህ ስም የሚያመለክተው በአብዛኛው ማንነቱን ሳይሆን የአገልግሎቱን ሁናቴ ነው የሚገለጸው። ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ የተሾመ ለአንድ ሥራና አገልግሎት ኃላፊነትን የተቀበለ የሚል ትርጉምን ያከተተ ነው።*

***□ሰው ል□*** *:- ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን በተወሰኑ ቦታዎች ተጠቅሶአል።መዝ8:4 ዳን7:13 ስለ ክርስቶስ በወንጌል መልዕክት ውስጥ የተጠራበት መንገድ ግን ፈፅሞ ከእነዚህ ሐሳቦች ይለያል እርሱ ሰብአዊነትን እንደ ተላበሰ ወይም ደግሞ ሰው እንደ ሆነ ለማመለከት ጌታም□ ራሱ የተጠቀመበት ገላጫ ስም ነው።ማቴ16:27 17:22 20:18,19,28 ማር8:38*

***□እግዚአብሔር ልጅ:-*** **(ወልት)** ክርስቶስ በምድር በነበረበት ወቅት ከብዙዎች ይጠብቅና ይፈልግ የነበረው ማንነት ይህ ነበር።□እርሱ □እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲያምኑና እንዲቀበሉ።ይህም ደግሞ ክርስቶስን ከእዚአብሔር ጋር እኩል አድርጎ መቀበል በሁሉ ዘንድ እጅግ ከባድ ስለ ነበር ነው።ከዚህ የተነሳ ይህ ቃል በተጠቀሱት ቦታዎች ሁሉ የሚያመለክተው የእርሱን ከአምላክ ጋር እኩል መሆንን ነው።ማቴ11:27,14:28-33,16:16,21:33-46,22:41-46,26:63 አብሮነት አስቀድሞ ይኖር የነበረው ከአባቱ ጋር መሆኑን፣የላከውም በአብሮነት ያለው አባቱ እንደሆነ፣ለልጅም ደግሞ በራሱ ስልጣን እንዳለው፣ሕይወት ለመስጠት፣ፍርድን ለመስጠት እንዲሁም በወልድ የሚያምን የዘላለምን ሕይወት እንደሚኖረው ሲናገር ለእግዚአብሔር ልጅ ወይም ለልጅ ተሰጥቶል እጸለ በእግዚአብሔር ሦሥትነት መሃል ያለውን እኩልነት የሚያመላክት በቀጥታ ያለሆነ ነገር ግን በተለዋጭ መንገድ ይገልጻል።

ይህንኑ ሐሳብ አጋንንቶችም የእግዚአብሔር ልጅ ሆጹ ልታሳድደን መጣህን እያሉ የበላይ ባለስልጣንነት ሲናገሩ □እርሱ ግን □እንዳይናገሩ ይከለክላቸው ነበር። ቴታ□በተፈተነም ሰዓት አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነህ ይህንን ድጋይ ዳቦ ሁን በለህ እዘዝ ብሎ ሲፈትነው እንመለከታለን።ይህ ሀሳብ

የሚያሳየን ይህን ያህል □እንደ እግዚአብሔር ከሆንህ ሁሉን ትችላልህና እሲቲ አሳይ ይህንን ማንነትህን ብሎ መፈቱኑ ነው:: □ሐ6:69 8:16,18,23 10:15,30 14:20

***አማኑኤል፦*** ለማሪጸም □□ ኛ ለዮሴፍ መላኩ ተገልጦ በነቢያት የተባለው ይፈጸም ዘንድ ስሙንም አማኑኤል ትሉታላችሁ አለው::ይህም በእርፅጥ አምላክ ከሰው ዘንድ ለረጅም ዘመን በሰዉ ሐጢያት ምክንያት ርቆ ሳለ አሁን ግን ሥጋን ለብሶ በሰው መካከል በመኖሩ የተሰጠው መግለጫ ስሙ ነው::ማቴ1:23

***ጌታ፦*** ጹህ ስም ለ□ርስቶስ ሲሰጥ ለእግዚአብሔር አብ ሲሰጥ እንደ ነበረው አዶናይ ከሚለው ቃል በተልዋጭ መንገድ ነው::አዶናይ የሚለው ቃል የሚገልጠው መሰረታዊው ትርጉም የበላይ፣ገዢ እና አምልኮአዊ አቀራረብን ሁሉ ያጠቃልላል::ስለ ሆነም ክርስቶስ መለኮታዊ ክብርን ሲሰጡት እንዲሁም የበላይነቱን ሲናገሩ ይጠቀሙበትና ማንነቱን ይገልጡበት ነበር::ማቴ21:3 24:42 ማር12:37,37 ሉቃ2:11,3:4 □ሐ□2:36 1ቆሮ12:3 □ሐ20:28

# 7. የክርስቶስ ስራዎች

## *ቅድመ ዘላለማዊነቱ*

- የመፍጠር ሥራ (ፈጣሪ ነው ክርስቶስ)

ክርስቶስ በቅድመ ማንነቱ ሲኖር ሳለ በሥጋ ከመገለጡ በፊት የሚያከናውነው ተግባር ነበረው ወይ? የሚል ጥያቄን ማንሳትና ለጥያቀውም ትክክለኛ መልስን መመለስ ተገቢ ነው::መጽሐፍ ቅዱስስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ሃሳብ አለው?

ዮሐንስ በወንጌሉ መጀመሪያ ስለ ቅድመ ሁናቴዉ ሲናገር አምላክ ሆኖ ከአባቱ ጋር እንደ ነበር ከተናገረ በኋላ በምድር ላይ ከሰማይ በታች ያለው ነገር ሁሉ ያለ እርሱ እንዳልተፈጠሩ ሁሉ ግን በእርሱ እንደተፈጠሩ ጸስረፅ□ል:: «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነው አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም::» ዮሐ1:3

ጳውሎስ በቆላስይስ መልዕከቱ ላይ ስለ ክርስቶስ ሥራ በቅደመ ሁኔ የነበረውን ሲገልጽ «... □ሚታዩትና □ማጁታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና...» ቆላ1:16

በዕብራዊያን መልዕክቱም ላይ ጳውሎስ በተጨማሪ የሚናረው ሐሳብ አለው:: «... ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን... » ዕብ1:2

ከእነዚህ ጥቅል ሐሳብ የምንረዳው እውነት ክርስቶስ በቅድመ ሕልውናው ያከናወነው ትልቁ ስራው የፈጣሪነቱ ስራ ነው::ይህም ደግሞ የመለኮትነቱን ክብርና ማንነት ይብልጥ አጉልቶ ያሳያል::

## በምድር ለ33 1/2 ሲኖር

ክርስቶስ በሥጋው ወራት ለ33 ዓመት ተኩል ሲመላለስ ያካናወናቸው ብዙ ሥራዎችም ቢኖሩትም እንኳ ከዋናው ወደ እዚህ ምድር ከመምጣቱ ጋር የሚዛመዱትን ብቻ መመልከቱ በቂ ይሆናል::መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ክርስቶስ ያደራጋቸውን ሁሉ አልመዘገበም ነገር ግን በስሙ አምነን ሕይወት ይሆንልን ዘንድ የተመረጡት ሪኮች ብቻ ተመዝግበዋል::ዮሐ20:30-31

ትኩረት ሰጥቶ ከሰራቸው ስራዎች መከከል

- ስብከቱ እና ትምህርቱ:-

ቴታ ጊዜውን በሰፊው የሰጠው አገልግሎቱ ነበር ማስተማር □እና መስበክ:: ብዙዉን ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በምሳሌ በማስተማር እነርሱን ሰማያዊ ዜጋ ለማድረግ ነበር ትኩረቱ::

ለምሳሌ:- የተራራው ስብከት ማቴ5-7
- ስለ ግብዝ ጻህፍት ፈሪሳዊያን ማቴ 23
- ስለ መጨረሻው ዘመን ማቴ 24
- ስለ እግዚአብሔር መንግስት ማቴ 13 እነዚህ ሰፋፊ ምዕራፎችን የወሰዱ የምንባብ ክፍሎች የክርስቶስ ትመህርቶች ነበሩ በወንጌል መጻህፍት ውስጥ::

- ታኣምራቱ:-

ክርስቶስ በአገልግሎቱ በሰዎች አለማመን ምክንያት ከልሆነ በስተቀር በብዙ ስፍራዎች ድንቅን □እና ታኣምራትን አድርጎል:: ጄህም □ፅሞ ስለ እርሱ ማንነት ሰዎች ትክክለኛ መረጽ እንዲኖራቸው አድርጓል::

- □ሐ2:1-11 በቃና ገሊላ በሠርግ ቤት ጌታ□ተገኝቶ ያደረገው ታኣምራት ማንነቱን ለደቀመዛሙርቱ የገለጠበት ነበር::«... ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ ክብሩንም ገለጠ □ቀመ□ሙርቱም በእርሱ አመኑ::» ምልክት ነበር ስለ ማንነቱ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመለከቱ በዚህም ምክንያት የገዛ ደቀመዛሙርቱ ማንነቱን በእርገጥ የሚያዉቁበት በር ተከፈተላቸው::
- ማቴ14:22-33 በባህር ላይ በማዕበልና በወጀብ ስትናወጥ ለነበረችው ታንኳ □እረፍት □እና ሰላምን ባመ□ ቴ□ □ቀመ□ሙርቱ በሙሉ «... በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት::» የመጣውን ለውጥ ብንመለከት ያደረገላቸው ታኣምራት ለእነርሱ በታንኳ ውስጥ ለነበሩት በአጠገባቸው ያለውን ጌታ ማንነት ነበር ያሳወቃቸው::

- ሌሎች ተጨማሪ ታአምራተን ሁሉ ወስደን ብንመለከት የእግዚአብሔርን ልጅ ማንነት እና □እግዚአብሔርን ማንነት ለሰው ልጆች ክርስቶስ ያሳየበት መንገድ ሆኖ ነበር ያለፈው::
  - ሞቱ:-

ቴታ ወደ ምድር ከመጣበት ዋና ምክንያት ስለ ሰዎች ልጆች በደልና ሀጢያት መስዋዕት ለመሆን ነው::በሞቱም በዙዎችን ወደ ራሱ ሰብስቧል:: ዮሐ12:24 «... የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች::» በዚህ ምክንያት ጌታ□እንደ ተጻፈለት ለመከራ □እና ለሞት ራሱን አሳልፎ ሰጠ::ሉቃ23:32-492

## ከትንሤዔዉ በኋላ

ክርስቶስ ኢየሱስ በቅድመ ሁናቴውና በሥጋው ወራት በዚህ ምደር ላይ ሲመላለስ ያካናውናቸው የነበረውን ሥራዎቹን አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ ተመልክተናል::በመቀጠል ደግሞ ዛሬስ ጌታ□ከትንሣዔዉ ማግስት ከሥራው አርፏል? ወይንስ ይሰራል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ አድርገን በማንሳት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር ያለውን እውነት መመልከት ተገቢ ነው::

ከሞት ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት እርሱ ራሱ ስለ መሆኑ በብዙ ማስረጃ ካሳያቸው በኋላ ስለ እርሱ እንዲመሰ□ሩ በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸውና የመንፈስ ቅዱስ ሀይልን እንደሚቀበሉ ተስፋን ከሰጣቸው በኋላ ወደ ሰማይ አርጎ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል:: □ሐ□1:1-11 ማር16:19-20

አስቀድሞ ወደ ነበረበት ክብሩ ከተመለሰም በኋላ ክርስቶስ ማንነቱ አልተለወጠም::ዛሬም ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ደግሞም ፍጹም ሰው ነው::ዮሐ17:4-5 በዚህም ምክንያት የሚያካናውነው <u>መለኮታዊ ሥራም</u> □ፅሞም <u>ቀጣይ መንፈሳዊ አገልግሎት</u> አለው::

- *መለኮታዊ ሰራዎቹ*
  - ✓ ጸሎትን የመስማትና የመመለስ ዮሐ14:14
  - ✓ ያመኑትን በመንፈቅ ቅዱስ የማጥመቅ □ሐ1:33
  - ✓ ለአማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መስጠት ኤፌ4:7
  - ✓ ቤተክርስቲያንን ማነጽ ወደ እርሱ ሙላት ልክ እንድትደርስ መንከባከብ ኤፌ1:22

- *መንፈሳዊ አገልግሎትን ማከናወን*
  - ✓ የማማለድ አገልግሎትን መፈጸም

- የዚህ አገልግሎት መሰረታዊው ትርጉም በአዲስ ኪዳን ብዙም አይታወቅም ነገር ግን በብሉይ ኪዳን በአይሁዶች ዘንድ በነበረው የመቅደስ አገልግሎት ምክንያት እንቅስቃሴው በመካከላቸው ስለ ነበር በትክክል ይታዉቃል:: በእኛ ዘንድ የመማለድ አገልግሎት ከትክክለኛ ግንዛቤ ውጪ ያደረገው የቃሉ መሰረታዊ የትርጉም አጠቃቀማችን መዛባት ነው::

- ይህን ቃል ስንጠቀም በአብዛኛው የምንጠቀምበት ትርጉም አንድ ወገንተኛ ለሌላኛው ወገን አምላክን ሲማጸን ሲለምን በያዘ መልኩ ነው የምንረዳው::ይህ ደግሞ ማንኛውም ሰዉ በቅርቡ ባለ ሰዉ አማከይኝነት የሚከናወን በመሆኑ በመንፈሳዊም ሆነ በምድራዊ የሕይወት አንቅስቃሴያችን ውስጥ ዘወትር የተለመደ ነው:: ይህም አንደኛዉ እና መደበኛው ትርጉም ነው::
- ሌላኛው ትርጉም ደግሞ በብሉይ ኪዳን እንደ አገልግሎት በሹመት ብቻ የሚገኝ በማንኛዉም ሰዉ ሊያከናውነው የማይችል በመንፈሳዊ ሥርዓት አምልኮ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ የአገልግሎት ቦታ□እና ስልጣን የሆነ በሰውና በእግዚአብሔር መከከል በሚፈጠረው በደል ምክንያት መከከለኛ ለመሆን በተደነገገው መለኮታዊ ስርዓት መስረት <u>የአስታራቂነትን አገልግሎት</u> ማከናውን እንጂ ልመና አይደለም::
- ለዚህ ትክክለኛው ምሳሌ የብልዩ ኪዳን የሊቀ ከህናቱ አገልግሎት ነው::አሮን ለዚህ አገልግሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሹመትን አግኝቷል::በዚህም መሰረት በዓመት አንድ ጊዜ ስለ ራሱ እና ስለ ሕዝቡ ሀጢያት መስዋትን ያቀርባል በዚህም በደል ይወገዳል::በተጨማሪም ለዚህ ትምህርት የመንፈልገው ሃሳብ ድንገተኛ በደል በሕዝቡ መካከል ቢከሰት እግዚአብሔር አምላክም ቢቆጣ እና መቅሰፍት በሕዝቡ መካከል ቢጀምር ሊቀ ከህኑ በመካከል እስካልገባ ድርስ መቅሰፍቱን የሚከለክል ወይም ሊያስቆም ሚችል የለም::ይህንን የማስቆም እና የማስከልከል ስራ እና ሹመት ነው <u>□ማማለት አገልግሎት ወይም መካከለኛ የመሆን ስልጣን ምንለው</u>:: □ኁ16:48,50
- በዚህ መሰረት ክርስቶስ ለአዲሱ ኪዳን አገልግሎት በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል የማማለድን አገልግሎት ሹመት ተቀብሏል::ዕብ8:6 5:6
- በቀድሞው ኪዳን በዙዎቹ ሞት ስለ ከለከላቸው በምትካቸው ሌላ ይተካል ክርስቶስ ግን ሞትን አንድ ጊዜ ስላሸነፈ የማይለወጥ ክህነት ያለው እርሱ ብቻ ሆኖአል::ዕብ6:23-25
- በቱ□ □ሙ ካስታረቀንም በኋላ ለየትኛውም በደል ወይም መቅሰፍት ለማስከልከል በእኛ እና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ የሆነ ለዘወትር ጣልቃ የሚገባ አንድ ያተመነ ሊቀ ካህን አለን እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ነው::1ጢሞ2:5
- ስለዚህ አግልግሎቱም ሐዋርያው ዮሐንስ ሲናገር ጠበቃ ይለዋል::1ዮሐ1:1«ልጆቼ ሆይ ሀጢያትን እንዳ□ታደርጉ ይህን □እጽፍላችኋላሁ:: ማንም ሀጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ *ጠበቃ* አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::□ርሱም □ሀጢጸታችን ማስተሰሪያ ነው...»
- ስለዚህ ክርስቶስ ብቻ እውነተኛ አማላጅ በሰው □እና በእግዚአብሔር በሆነው ጉዳይ ላይ ጣልቃ ለመግባት ሙሉ ሹመት እንዲሁም ስልጣንን የተቀበለ ሆኖ ዛሬ በሰማይ ስለ እኛ ጁታይልናል::አሜን!

# ፰.አስተምህሮ ክርስቶስን አስመልክቶ በተሳሰበተ የአተረጓጎም ምክንያት በተለየ ፍቺ የሚታዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

ስለ ክርስቶስ ማንነት በተመለከተ ብዙ የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም አሰጣጥ ከመኖሩ የተነሳ በክርስትና አስተምህሮ ላይ የተለያዩ የስህተት አመላከቶችን አሳድጓል ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን መመልከት እንችላለን።

➔ ቆላ1:15-16 «... ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ... »

- ይህ አባባል በተሳሳተ መልኩ ስንጠም እርሱ በመጀመሪያ የተፈጠረ በመቀጠለ ሌሎችን ደግሞ ከዚያ በኋላ በእርሱ ተ□ቷሩ አምላክ ሳይሆን የመጀመሪያ ፍጡር የሆነ ሰው ነው።የሚል የስህተት አተረጓጎም ነው።
- ትክክለኛው ግን እርሱ ከፍጥረት ሁሉ መከከል ከፍ ያለ የተከበረ ለማለት ነው። ቢሆንም ግን የተለያዩ ዓይነት የቃላት አጠቃቀሞች እንደ አውደምንባቡ ሊለያይ ስለ ሚችል ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ:- ሉቃ2:7 ... የበኩር ልጇንም ወለደች... የመጀመሪያዋን ለማለት ሲሆን

- ሮሜ8:29 ... በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር... የሁሉ ታላቅ □በላጩ ለማለት ሲሆን
- ራዕ1:15 ... ከሙታን በኩር... ከሞት በመነሳት የመጀመሪያ ነው ለማለት ሲሆን

በመፈጠር የመጀመሪያው ነው ሳይሆን አጠቃላዩ ሐተታ□እርሱ ከፍጥረት በፊት የነበረ የሁሉ አለቃ □በላጩ ራስ ለማለት ተፈልጎ የተሰጠ አገላለጽ ነው።

➔ ዮሐ14:28 «... አብ ከእኔ ይበልጣልና ...»

- በተሳሳተ መልኩ ስንጠቀመው ሊይዘው የምንችለው ሃሳብ በዚህ ንግግሩ በማንነት ደረጃ ወልደ ከአብ ያንሳል።ስለዚህ አምላክ አድረገን ልናመልከው አይገባም አልያም ልናየው አንችልም።
- ነገር ግን ለማለት የፈለገው ጌታ በንግግሩ በሥጋው ወራቱ የባሪያን መልክ በመያዝ ክብሩን ትቷል ኘል2:1-11 ይሁን □እንጂ የመለኮት ሙላት በሰውነቱ ተልጦ ይኖራል።ቆላ2:9 ስለሆነም በማንነቱ ክርስቶስ ከአብ አያንስም። በሥራ □መ□ □በላጩ የበታችነት እንጂ በማንነት የመጣ አይደል።

➔ 1ቆሮ11:3 «... የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር ነው ...»


- ይህ ሃሳብ በተሳሳተ መልኩ ስንጠቀመው አሁንም በድጋሚ ክርስቶስ በማንነቱ ከአብ እኩል እንዳይደለ ማስረጃ አድርገን ልናቀርብ እንችላለን።
- ይሁን እንጂ በስራ የመጣ የሥራ ክፍፍልን የሚያሳይ አገላለጥ ነው። ማለትም አብ የፈቃድ ባለቤት ሆኖ ለወልድ ትእ□□ ሲሰጣ እንደ በላይ አስተዳዳሪ ወልድ ደግሞ እንደ ተግባሪ የተሰጠውን ሀላፊነት ሲወ□ ጸመለ□ታል እንጂ በማንነት ደረጃ ወልድ ዓምላክ አይ□ለም የሚያስብል አባባል ያዘለ አይደለም።
- ጁህ □በላጁ እና የበታች የሚመስል ግንኙት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከተው በስራ ክአአል የመጣ የግንኙነት ሰንሰለት አንጂ የማንነት መግለጫ ዓረፍተ ነገር አይደለም።

➔ **1ቆሮ15:28 «... ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል ...»**

- በተመሳሳይ መልኩ ይህን ቃል በመጠቀም የክርስቶስን ማንነት ከጥያቄ ውስጥ በማስገባት እስከ መጨረሻው ክርስቶስ ለእግዚአብሔር አብ ተገዝቶ ስለ ሚኖር በማንነቱ ከአብ ያንሳል።
- እንግዲህ ከላይ ለማሳየት እንደ ተሞከረው ክርስቶስ ከአብ እንዳነሰ አድርገን እንድናስብ የሚያስገድዱን የሚመስሉ የንባብ ክፍሎችን ስንመለከት ይህ አባባለቸው በአብዛኛው በስራ የመጣን ግንኙነትን አንጂ በማንነት ላይ ያነጣጠረ ሃሳብን እንደማያንጸባርቁ ተመልክናል አሁን ደግሞ በክርስቶስ ሲከናወኑ የነበሩ የድነት ተግባራት ሁሉም ነገር ወደ ፍጻሜ ከደረሰ □እና የመጨረሻው ጠላት ሞት ከተገዛለት በኋላ የነገር ፍጻሜ ይሆናል በሌላ አባባል በክርስቶስ የተጀመሩ ሀላፊነቶች ሲጠናቀቁ ።ከዚህ በኋላ የስራ ክፍፍል የሚባል ሐሳቡም ሆነ ተግባሩ ስለ ማይኖር እግዚአብሐር ሁሉ በሁሉ ይሆናል።የሚል ሃሳብ ይይዛል።

➔ **ማር13:32 «... ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም...»**

- ይህ ጥቅስ በተሳሳተ መልኩ ስንጠቀምበት የሚያመለክተው ሐሳብ ክርስቶስ ውስን ማንነት ስላለው በዕውቀት ደረጃ የማያውቀው ነገረ አለ።ስለሆነም እርሱ ዓምላክ አይደለም።
- ነገር ግን ክርስቶስ ለማለት የፈለገው ሁሉ ነገር እንደ አብ ፈቃድ የሚሆን እና የሚከናውን ነው ለማለት ሲሆን እንዱሁም እርሱ ሰው ስለ መሆኑ ይበልጥ ትኩረት እንዲሠጡት ለማድረግ ነው።በዕውቀት ደረጃ ክርስቶስ ስለ ሰው ማንም ሊነገረው እንደ ማያስፈልግ ነገር ግን ሁሉን እንደ ሚጸዉቅ በተለጸ ቦታ□ ጊዜ አሳይቶአል።



# ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለዓለም የተባረከ ጌታ እና አምላክ ነው!